ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 237 ሚያዝያ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትሪያርክ



ብፁእ ካርዲናል አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ



ፓስተር ጻዲቁ አብዶ



ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ

# ምዕመናን በዓሉን በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመደገፍ እንዲያከብሩ የኃይማኖት አባቶች አሳሰቡ

**ሄለን ወንድምነው፣ ዳግማዊት አበበና ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሳኤ በዓል ሲያከብር በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን በመደገፍ ሊሆን እንደሚገባ የኃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የትንሳዔ በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ በዓለ ትንሣዔ የእግዚብሔር ፍቅር መገለጫና የተስፋችን ማሳያ ነው፡፡ ይህን በመገንዘብ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ልጆች ደኅንነት በአንድነት በመቆም ለተራቡት፣ ለተጠሙት፣ ለታረዙት፣ ለታመሙትና ለታሰሩትም ሁሉ ካለን ከፍለን በመስጠት በዓለ ትንሣዔውን ማክበር ይገባል፡፡

በእግዚአብሔር አሠራር ኃጢአት ያለ ቤዛነት አይሰረይም፤

ምዕመናን በዓሉን...ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ‹‹ከአጭሩ ሕማማት በኋላ ረዥሙ የኢትዮጵያ ትንሣዔ ይመጣል››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከአጭሩ ሕማማት በኋላ ረዥሙ የኢትዮጵያ ትንሣዔ የሚመጣ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ2016 ዓ.ም የትንሣዔ በዓል አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ሕማማት አጭርና ከባድ ቢሆንም ሕማማቱን ለማለፍ የሚያስችል ኃይል አላት፡፡ ከአጭሩ ሕማማት በኋላ ረዥሙ የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚመጣ ይሆናል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ሞት፣ ግፍና ሙስናን፣ ሲዖልና መቃብርን አሸንፎ የተነሣበትን የትንሣዔ በዓል በየዓመቱ እናከብራለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሰሞኑ ሕማማት ፈተናን፣ ስቃይን፣ ክህደትን፣ አሳልፎ መስጠትንና የከፉዎችን ኅብረት በጽናት ያለፉ ትንሳዔውን ለማየት ችለዋል ብለዋል፡፡

‹‹ከአጭሩ ሕማማት...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በመዲናዋ ባለፋት ዘጠኝ ወራት ከ6 ሺህ 700 በላይ የአቅመ ደካማ ቤቶች ተገንብተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ 6 ሺህ 700 በላይ የአቅመ ደካማ ቤቶች መገንባታቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተገኙበት በአዲስ ከተማና አራዳ ክፍለ ከተማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ዜጎች የመኖሪያ ቤቶችን የማስተላለፍና አዲስ ግንባታ የማስጀመር መርሃግብር ትናንት ተካሂዷል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በመርሃግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በዘንድሮው ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ 6 ሺህ 700 በላይ የአቅመ ደካማ ቤቶች ተገንብተዋል። በትንሳዔ በዓል ዋዜማ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች 907 መኖሪያ ቤቶች ለነዋሪዎች ተላልፈዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት በርካታ የመኖሪያ ቤቶች

በመዲናዋ ባለፋት ዘጠኝ ወራት...ወደ ገጽ 4 ዞሯል




















**‹‹ የተረከብናቸውን ድሎች ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል››**

- ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን
የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት

ገጽ 4



ዜና

# የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ለትንሳዔ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ለትንሳዔ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ለትንሳዔ በዓል ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ የትንሳዔ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ በመስቀል ላይ እስከሞት ድረስ ራሱን አሳልፎ በመስጠት ወደር የለሽ ፅኑ ፍቅር ያሳየበት እና እንዲሁም ለበደሉት ሳይቀር ይቅርታና ምህረትን የሰጠበት፣ ሞትንም ድል ያደረገበት መታሰቢያ በዓል ነው።እኛም እርስ በርሳችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሁሉንም ሰው በመውደድ፣ በይቅርታ፣ በምህረትና በመረዳዳት እንድንኖር ፈጣሪ ይርዳን። በዚህ በኩል ለተዳከሙ እሴቶቻችንም ትንሳዔ ይሁን ነው ያሉት።

የአማራ ክልል ርእሰ መሥተዳድር አቶ አረጋ ከበደ በትንሳዔ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለብዙዎች ቤዛ ሆኖ ሞትንም ድል አድርጎ በመነሳቱ ለሠው ልጆች ፍቅርን፣ እርስ በርስ መዋደድን፣ ሠላምና ለነፃነት ራስን መስዋዕት መሆንን ቤዛና አብነት ሆኖ አሳይቶናል።

በዓሉ ሲከበር በታላቁ መጽሐፍ እንደታዘዘው ሁሉም ሰው ልቦናውን ለምህረት፣ ለይቅርታና ለእርቅ በማዘጋጀት በልዩ ልዩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን በማገዝ እጆቻችንን ለድጋፍ በመዘርጋት ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የትንሣኤ በዓል ባስተላለፉት መልዕክት ላይ እንደገለጹት፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የተቀደሰ ሕይወት ምልክትና በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ውድ ስጦታ ተደርጎ እንደሚታመን ገልጸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሔደበትን መንገድ፣ ያሳየንን ፍቅር እና ሰላም፣ ዝቅ ብሎ ያገለገለበትን ትህትና፣ በፍቅር እና በትዕግሥት መቻቻልን እንዲሁም ሁሉንም ሰው ማክበርን የመሳሰሉ ምሳሌዎቹን መከተል ከሁላችንም ይጠበቃል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው በበኩላቸው ያለፉት የፆምና የፀሎት ጊዜያት በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ መንፈሳዊ ሕይወትን በማደስ ፈሪሃ እግዚአብሔርን የተላበሰ ስብዕና እንዲሁም ሞራላዊ እሴትን ለማጠናከር ጉልህ ሚና የተጫወቱ ናቸው ብለዋል።

በፆሙ ጊዜያት የጎለበቱት መልካም ተግባራት የአብሮነትን ድልድይ የሚያጠናክሩና መልካምነትን የሚያላብሱ፣ በመሆናቸው የዘወትር የተግባር መርሆዎች ሆነው እንዲቀጥሉ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል። የትንሳዔን በዓል ስናከብር የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህላችንን በማጠናከር መሆን እንዳለበት የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሃር ገልጸዋል። ከንቲባ ከድር ለትንሳዔ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ የመልካም ምኞት መልዕክት አስተላልፈዋል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ የትንሳዔ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፅኑ ፍቅር በመስቀል ላይ ያሳየበት እንዲሁም ይቅርታና ምህረትን ለሰው ልጆች የሰጠበት የጥልና የመለያየት ግድግዳን አፍርሶ የሰውን ልጅ የታደገበት ነው፡፡

የትንሳዔ በዓል መታዘዝን፣ ይቅርታንና ምህረትን እንዲሁም አንዱ ለሌላው መተሳሰብ እንዳለበት የሚያስተምረን ሲሆን መረዳዳትንና መጠያየቅን ከተለመደው ባህል ባለፈ በፍጹም መንፈሳዊነት በጎዳና የወደቁትን በማሰብ፣ በሕግ ጥላ ስር ያሉትን በመጠየቅ፣ታመው የተኙትን በማጽናናት በማካፈል በአብሮነት ማክበር ይገባል ብለዋል፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ በበኩላቸው የትንሳዔ በዓል በክርስትና እምነት ጥልቅ ትርጉም ያለው፤ ክርስቶስ የአዳምን ዘር ከበደል ቀንበር ነፃ ያወጣበት፤ ለሰው ልጆች ምሕረትና ድኅነት፤ ሰላምና ፍቅር የተገኘበት ነው፡፡

ትንሣዔ የጽናት፤ የተስፋና የድል በዓል በመሆኑ በዓሉ ሲከበርም በየወቅቱ የሚገጥሙ ጊዜያዊና ተለዋዋጭ ፈተናዎች በፅናት በማለፍ ለቀጣይ ድል መብቃት እንደሚቻል በማሰብ ሊሆን ይገባል።

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ በበኩላቸው የትንሳዔ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆች ሃጢአትና በደል በመሻር በቀራንዮ መስቀል ነብሱን እስከ መስጠት ለሰው ልጆች መስዋዕት የሆነበት በመሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ሆኖ በተግባር ባሳየን ትህትናና ፍቅር መሠረት ከግላዊ ጥቅምና ፍላጎት በመላቀቅ እርስ በእርስ በመተጋገዝና በመተሳሰብ ሕዝባዊ ጥቅምን ማስቀደም እንዲሁም ለችግሮችና ለፈተናዎች ሳንበገር የሀገሪቱን የብልፅግና ትንሳዔ ማፋጠን ያስፈልጋል ብለዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን በበኩላቸው የትንሣዔ በዓል በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሠውን ልጅ ለማዳን መከራ ተቀብሎ በመስቀል ተሰቅሎ፣ ሞቶ መነሣቱን በመዘከር የሚያከብሩት በዓል መሆኑን ገልጸዋል።

የእምነቱ ተከታዮች በዓሉን ሲያከብሩ ኃይማኖታዊ አስተምህሮውን በመከተል በሀገራችን ያለው የመከባበር፣ የአብሮነትና የመረዳዳት መልካም እሴት የበለጠ እንዲጎለብት የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ ህዝበ ክርስቲያኑ በአብይ ጾም ወቅት ሲያደርጓቸው የነበሩትን የመደጋገፍና የመተዛዘን ተግባራት ከጾም ፍቺም በኋላ አጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።



ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

# ትንሳዔ ይቅርታንና ምህረትን የምንማርበት በዓል ነው

*መዓዛ ማሞ*

አዲስ አበባ፡- የትንሳዔ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅርታና ምህረትን ለሰው ልጆች የሰጠበት፤ የጥልና የመለያየት ግድግዳን አፍርሶ ፍቅርን ያሳየበት በዓል መሆኑን ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ ተናገሩ፡፡

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ትንሳዔ በዓል ክርስቶስ ከሞት የተነሳበት በመሆኑ የበዓላት ሁሉ በኩር እና የአማኞች የወደፊት ተስፋ የሚያረጋግጥ በዓል ነው ፡፡

የትንሳዔ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፅኑ ፍቅር በመስቀል ላይ ያሳየበት እንዲሁም ይቅርታና ምህረትን ለሰው ልጆች የሰጠበት፤ የጥልና የመለያየት ግድግዳን አፍርሶ የሰውን ልጅ የወደፊት ተስፋ ያረጋገጠበት መሆኑን አውስተዋል፡፡

በዓሉ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩት መንፈሳዊ በዓላት አንዱ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡

ይህ የትንሳዔ በዓል መታዘዝን፣ ይቅርታንና ምህረትን እንዲሁም አንዱ ለሌላው መተሳሰብ እንዳለበት የሚያስተምር መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

በዓሉን ስናከብር መረዳዳትንና መጠያየቅን ከተለመደው ባህል ባለፈ በፍጹም መንፈሳዊነት ስሜት በጎዳና ላይ የወደቁትን በማሰብ፣ ታመው የተኙትን በማጽናናትና ካለን ላይ በማካፈልና በአብሮነት መሆን እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች በደል ተላልፎ በመሰጠት የሰውን ልጆች ከጨለማ ወደ ብርሃን ነጻ ለማውጣት ዋጋ የከፈለበት በመሆኑ እኛም አቅመ ደካሞችን በመርዳትና ካለን በማካፈል፣ ለወገኖቻችን በመድረስና በመተሳሰብ በዓሉን ማክበር አለብን ነው ያሉት፡፡

ትንሳዔ የክርስትና ዋነኛው ማዕከልና ሰንደቅ ዓላማው የሆነ በዓል መሆኑን ገልጸው፤ በዓሉ ከሌሎች ሁሉ በዓላት ከፍ ብሎ የሚከበር በዓል መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ሰሞነ ህማማት ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት የነበረውን ብሉይ ኪዳንን የሚወክል የአንድ ሳምንት ጊዜ መሆኑን አመላክተው፤ በሰሞነ ህማማት አማኞች ብሉይ ኪዳን በዓመተ ፍዳ እንዳሉ በማሰብ መስቀል ባለመሳለም፣ እስከ ምሽት በመጾም፣ የክርስቶስ መከራ፣ ሞትና ህመሙን እንደሚያስቡበት ገልጸዋል፡፡

የክርስቶስ መከራ ከሐሙስ እንደሚጀምር ተናግረው፤ በእለቱ በጌቴሴማኒ እየጸለየ ሳለ ከተያዘበት ሰዓት አንስቶ እስከ ማግስቱ 11 ሰዓት ድረስ መከራን ያለማቋረጥ ለ20 ሰዓታት ተቀብሏል ብለዋል፡፡

እንደ ዲያቆን ኃይሌ ገለጻ፤ ክርስቶስ ሁለት ፍርድ ቤቶች ቀርቧል፡፡ በለሊት የአይሁድ ሸንጎ ላይ ቀርቦ ተይዞ ምስክር ተፈልጎበታል፡፡ ብዙ መከራ፣ ግፍ እየተፈጸመበትና እየተተፋበት በጉድጓድ ውስጥ ሌሊቱን አሳልፏል፡፡

በማግስቱም የቄሳርን መንግሥት፣ ግብርን አትክፈሉ ይላል በማለት የሀሰት ክሶችን አቅርበው በቄሳር ፊት እንደከሰሱት ተናግረው፤ አማኞች ሰሞነ ሕማማትን የክርስቶስን ስቃይ እያሰቡ እንደሚያሳልፉ አስረድተዋል፡፡

ክርስቶስ በሶስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ተናግረው ፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች የትንሳዔ በዓልን ሲያከብሩ ጌታ እርቃኑን በሆነ ጊዜ እንደገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ እርቃናቸውን የሆኑ ሰዎችን በማልበስ እና የተቸገሩ ሰዎችን ካላቸው በማካፈል እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# “የበጎነት ተግባራት በበዓል ቀናት ብቻ ተወስነው ሲቀሩ አይገባም”

-አቶ ቢንያም በለጠ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የበጎነት ተግባራት በበዓል ቀናት ብቻ ተወስነው ሊቀሩ እንደማይገባ የመቄዶንያ የአእምሮ ህሙማንና አረጋውያን መርጃ ማዕከል መስራች አቶ ቢንያም በለጠ ገለፁ።

አቶ ቢንያም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የትንሳዔ በዓል እንኳን አደረሳችሁ መልዕክቱን አስተላልፈው፤ በበዓል ቀናት የሚስተዋሉ የመረዳዳት፣ የመተዛዘንና የመደጋገፍ ተግባራት መልካም ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የበጎነት ሥራዎችን ለመከወን ቀን እየጠበቁ ሳይሆን የሁልጊዜም ተግባር ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ቢንያም፤ የመረዳዳት ልምዱን ቋሚ አድርጎ መቀጠል እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በሁሉም ኃይማኖቶች በበዓል ወቅት ትብብር ማድረግና አቅመ ደካሞችን መርዳት መልካም ቢሆንም ችግረኞች ግን ሁልጊዜም ስላሉ በዘላቂነት መደገፍ እንጂ የመልካምነት ተግባራት በዓመት ሁለትና ሶስት ቀናት ብቻ ተወስነው ሊቀሩ አይገባም ብለዋል።

በክርስትና እምነት አስተምህሮ መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ዋጋን ሰጥቷልና የእምነቱ ተከታዮች ደግሞ ስለ መልካምነት የሚከፈል መስዋዕትነትን እለት እለት መክፈል ይገባቸዋል ሲሉ አቶ ቢንያም ተናግረዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሆኖ ሰው መሆንን ሳይፀየፍና ሳይንቅ ወደ ምድር ወርዶ እስከ ሞት በደረሰ ፍቅር ለሰዎች መልካም ከሆነ የሰው ልጅ ደግሞ እርስ በርስ በመደጋገፍና በመረዳዳት አንዱ ለአንዱ ሊኖር እንደሚገባው አቶ ቢንያም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከበጎነት ርምጃዎች ዋነኛውና የመጀመሪያው ሰዎችን አለመጉዳት ነው ያሉት አቶ ቢንያም፤ በቀጣይም ከዚያ አልፎም ለሰው መኖር መቻልና ችግረኞች ቋሚ ድጋፍ እንዲኖራቸው መሥራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝቧል።



አቶ ቢንያም እንዳመላከቱት፤ በሀገሪቷ በተለያዩ ምክንያቶች በርካታ ሰዎች በየቤታቸው የተለያዩ ችግሮችን እያስተናገዱ ይገኛል። በበሽታ የተያዙ የአልጋ ቁራኛዎች፣ ጎዳና ላይ የተፈናቀሉ በቤተሰብ ደረጃ የሰው ፍቅርና መፅናናትን የሚሹ አሉ እነዚህን በየቀኑ መጠየቅና ማገዝ ያሻል ብለዋል። እንደ መቄዶንያ ያሉ የመርጃ ማዕከላትን መደገፍም ከመላው ሕዝብ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል።

የበጎነት ሥራዎች ሰማያዊ ዋጋንም ጭምር የሚያሰጡ ናቸው ያሉት አቶ ቢንያም ያንን ምድራዊ ርካታንና ሰማያዊ ዋጋን ለማግኘት ሁልጊዜ በበጎነት መንገድ መበርታት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

አቶ ቢንያም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የትንሳዔ በዓል እንኳን አደረሳችሁ መልእክቱን በማስተላለፍ ለመቄዶንያ የድጋፍ ጥሪውንም አስተላልፏል።

ከአዲስ አበባ ውጪ 27 ቅርንጫፎች ያሉት መቄዶንያ የአዕምሮ ህሙማንና አረጋውያን መርጃ ማዕከልም ለበርካታ ተረጂዎቹ በየቀኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ የሚያደርግ በመሆኑ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ትብብር የሚጠይቅ መሆኑንም አቶ ቢንያም ገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መልካም የትንሳዔ በዓል!

እንደ ክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ የትንሳዔ በዓል ስለሰው ልጆች ሃጢያት በቀራኒዮ መስቀል ላይ ሕይወቱን የሰጠው መድሃኒት፣ ጌታ እና አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ በትንሳዔ የድል መንፈስ የተነሳበትን ቀን ለማስታወስ የሚከበር አጅግ ታላቅ በዓል ነው። ትንሳዔ የድል እና የመነሳት በዓል ነው ።

ዕለቱ ከዚህም ባለፈ በሰው እና በፈጣሪ መካከል በሰዎች አለመታዘዝ ምክንያት የተፈጠረው መለያየት ፤በእርቅ የተቋጨበት ፤የሰው ልጅ የቀደመ ጥፋቱም በክርስቶስ በሆነ ቤዛነት የተሻረበት፤ በአዲስ ሕይወት ፣በትንሳዔው መንፈስ የዘላለም ሕይወት የተጎናጸፈበትና ሰማያዊ ዕድል ያገኘበት ፣ የአዲስ ታሪክ ትርክት ጅማሬ ነው።

ቀኑ እንዲመጣ ክርስቶስ በጭለማ ሃሳብ ተፈትኗል ፣በብዙ ተወግዟል ፣በብዙ ተብጠልጥሏል፤ ተሰድቧል ፤ ተተፍቶበታል ፣ በብዙ ተከዷል፤ ተገርፏል፤ ተሰቅሏል፡፡ ብዙ ብዙ መከራን ተቀብሏል፡፡ ይሁንና ስለፍጻሜው የተስፋ ብስራት ሲል ሁሉን ተቀብሏል። ራሱን ዝቅ ዝቅ አድርጎ የመስቀልን ሞት ተቀብሏል። በዚህም በጨለማ ለሚኖሩ አዲስ የብርሃን ወገጋገን ሆኗል።

ትንሳኤ ብርሃን ነው፡፡ ከብዙ ጨለማና ጭለማ ከወለደው ድንግዝግዝ በኋላ የመጣ ንጋትም ነው። ብዙ ውጣ ውረዶች በርትተው ተስፋ መቁረጥ በበዛበት የተገኘ የተስፋ ብስራት አዋጅም ነው። ከዚህም ባለፈ ትንሳዔ ተስፋቢስነትን ፍጹም ወደሆነ ተስፋ የለወጠ ነው ፡፡

ከመከራ በኋላ ትንሳዔ ሁልጊዜም አለ፡፡ ከጨለማ በኋላ የሚነጋ ቀን አለ፡፡ ትንሳኤ ከሀገራችን አሁናዊ እውነታ ጋር የሚነጻጸር ነው፡፡ ሀገራችን በብዙ ፈተናዎች፣ በብዙ ውጣውረድ ውስጥ እያለፈች ነው፡፡ እነዚህ ውጣ ውረዶች የትንሳዔያችን አብሳሪዎች ናቸው ።

አሁናዊ ሀገራዊ እውነታችን ፣ ከትንሳዔ በፊት ካለው ጊዜ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ እያለፍንበት ያለውም ጊዜ ወደትንሳዔያችን እየተቃረብን እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ እንደሀገር ስለተስፋችን እየከፈልን ያለው ዋጋ የነገ ትንሳዔ አብሳሪ ጉልበታችን ነው ፡፡

ጌታ ኢየሱስን ለመያዝ፣ ለማሰቃየት፣ ለመግረፍ፣ ለመስቀል የተሴረው ሴራ ከሀገራችን አዋኪ ትርክቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡

ይሁዳ እየሱስን እንደሚወደው የውሸት ሲስመው፣ በኋላም በሰላሳ ዲናር አሳልፎ ሲሸጠው፣ ይሄን ከሀገር በልተው ወጪት ሰባሪ የሆኑ ግለሰቦችን ያስታውሰናል ፡፡ በአንድ ሌሊት የጴጥሮስ ክህደት፣ የነይሁዳ ወጥቶ መቅረት ያመኑ መስለው ሀገር የከዱን ያመላክተናል፡፡

ከመስቀሉ ስር ያልተለዩት እንደነ ዮሃንስ አይነቶቹ ደግሞ ለሀገር ታምነው፣ በእውነትና በጽናት የቆሙትን ሰብዐ ፍጡሮችን ያስታውሱናል፡፡ ከዚህ ሁሉ የማይነጋ ከሚመስል አስጨናቂ ለሊት በኋላ እንደሀገር ጭለማችን እየነጋ ነው፡፡ የማያልፍ ከመሰለ ወጀብ እየወጣን መሻታችንን ለመጨበጥ እየተንጠራራን ነው።

ትንሳዔ ከዚህም ባለፈ ከጨለማ ወደብርሃን፣ ከዝቅታ ወደከፍታ፣ ከሽንፈት ወደ ድል የሚወስድ መንገድም ነው፡፡ በሀገራችን እና በሕዝባችን ላይ እየሆነ ያለው ሰላም ማጣት፣ ስደትና መከራ ከትንሳዔ በፊት እንዳሉ የክርስቶስ ዘመኖች ናቸው፡፡ ለማያልፍ የተስፋ ቀን ለመታጨት በወጀቡ መሀል መሄድ ግድ ነው ፡፡

"ዘ ወረደ" ብለን ሆሳዕና ላይ ስንደርስ ፣ መነሻችን ውጣ ውረድ ቢሆንም፣ መድረሻችን ግን ትንሳዔ ነው፡፡ መከራዎቻችን ለምንጠብቀው ትንሳዔያችን /መነሳታችን ጉልበት ሆነው ድል ሊያቀናጁን ከበር አድርሰውናል፣ የመጨረሻ መስመር ላይ አቁመውናል።

የትንሳዔያችን ጀምበር ምስራቅ አድማስ ላይ እየወጣች ነው፡፡ ትንሳዔያችንን የማዋለድ ምጥ ሲያበቃ ያን ጊዜ የኢትዮጵያ አበሳዎች እንደጉም ይተናሉ፡፡ ትንሳዔዋም ከቃልነት አልፎ የሚጨበጥ እውነት ይሆናል። መልካም የትንሳዔ በዓል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# "ብርቱውን ይዘናል - እንበረታለን፤ ኃይል በሚሰጠው እንታመናለን"

\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

/ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የትንሳኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ሙሉ ቃል /



**የተነሣነው**
**ኢትዮጵያ እንደምትፈተን ዐውቀንም፤ አምነንም ነው። ለዘመናት የኖሩ ስብራቶችንና ብልሽቶችን ልናክም ስንነሣ መንገዱ አልጋ በአልጋ አይሆንም። ከችግሩ ማትረፍ የለመዱ አካላት ዝም አይሉም፤ ኢትዮጵያ በማሽን እንደሚረዳ ሕመምተኛ ሆና በሞትና በሕይወት መካከል እንድትኖር የሚፈልጉ ኃይሎች ዐርፈው አይቀመጡም**

እንኳን ለ2016 ዓ.ም የትንሣኤ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ሞት፤ ግፍና ሙስናን፤ ሲዖልና መቃብርን አሸንፎ የተነሣበትን የትንሣኤ በዓል በየዓመቱ እናከብራለን። ከበዓሉ በፊት የሕማማትን ሰሞን እናሳልፋለን። ሰሞነ ሕማማቱ ፈተናን፣ ስቃይን፣ ክህደትን፣ አሳልፎ መስጠትን፣ የክፉዎችን ኅብረት፣ የምናስብበት ነው። ሐሰት ያሸነፈች፣ እውነት የተሸነፈች መስላ የታየችበት ነው። ብዙዎች መሥዋዕትነትን ፈርተው የሸሹበት ነው። አንዳንዶችን የሚያልፍ ጎርፍ ወሰዳቸው፤ አንዳንዶችን የሚሰክን ማዕበል ነጠቃቸው። ጥቂቶች ከሕማማቱ አልፈው ትንሣኤውን ለመመልከት ቻሉ።

የከተማው ጩኸት እና የሐሰቱ ወሬ እንኳን በሩቅ የነበሩትን፣ ቅርብ የነበሩትንም አሸንፏቸዋል። የሆሳዕና ዕለት ደግፈው የወጡት ከሦስት ቀን በኋላ ሊቃወሙ ሲወጡ ምንም አልመሰላቸውም። ድጋፋቸውም ተቃውሟቸውም ሁለቱም የጥቅም እንጂ የመርሕ አልነበረም። ሁለቱም ከእውነታው የተጣሉ ነበሩ። ሕማማት የውስጥና የውጭ ጠላቶች ተባብረውበታል። በሌላ ጊዜ ለሞት የሚፈላለጉ አካላት እውነትን ለመስቀል ሲሉ ግን ተባብረው ቆመዋል።

ሰዎቹ ያልተረዱት አንድ እውነታ ነበር። ከሕማማቱ ይልቅ ትንሣኤው ይበልጣል፤ ይረዝማልም። ሕማማቱ አምስት ቀን ሲሆን ትንሣኤው ግን አስር እጥፍ ይሆናል። የአምስት ቀን ፈተና የሃምሳ ቀን ዋጋ አለው። በርግጥ የሕማማቱን ሽብርና ዋይታ፣ መከራና እንግልት ለተመለከተ ትንሣኤ የሚመጣ አይመስለውም። ትንሣኤው ግን የታመነና የተረጋገጠ ነው። የበለጠ ማረጋገጥ የሚቻለውም ጸንቶ እንደ ዮሐንስ በመቆም ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ እያለፈች ነው። በፈተና ውስጥ የቆመች ሀገር ግን አይደለችም። በፈተና ውስጥ እያለፈች ያለች እንጂ። ወቅቱ ለኢትዮጵያ የሕማማት ሰሞን ይሆን ይሆናል። አራት ነገሮች ግን እውነት ናቸው። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕማማት አጭር መሆኑ፤ ሁለተኛው አጭር ቢሆንም ከባድ መሆኑ፤ ሦስተኛው ኢትዮጵያ ሕማማቱን ለማለፍ የሚያስችል ኃይል ያላት መሆኑ፤ አራተኛው ከአጭሩ ሕማማት በኋላ ረዥሙ የኢትዮጵያ ትንሣኤ የሚመጣ መሆኑ ነው።

የተነሣነው ኢትዮጵያ እንደምትፈተን ዐውቀንም፤ አምነንም ነው። ለዘመናት የኖሩ ስብራቶችንና ብልሽቶችን ልናክም ስንነሣ መንገዱ አልጋ በአልጋ አይሆንም። ከችግሩ ማትረፍ የለመዱ አካላት ዝም አይሉም፤ ኢትዮጵያ በማሽን እንደሚረዳ ሕመምተኛ ሆና በሞትና በሕይወት መካከል እንድትኖር የሚፈልጉ ኃይሎች ዐርፈው አይቀመጡም። ግን ሕማማቱን እኛ ካልተቀበልንላት ለኢትዮጵያ ማን ይቀበልላታል? የመከራውን ቀንበር ካልተሸከምንላት የሀገር ልጅነቱ የቱ ጋ ነው። "ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ" እያሉ በስሟ ሲምሉ የነበሩ ብዙዎች ነበሩ፤ ከልባቸው ለቃላቸው ታምነው ልጅ የሆኗት ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። አንዳንዶች በስሟ የሚገዘቱት እንጀራዋን ለመብላት እንጂ መከራዋን ለመካፈል አይደለም፤ በተቃራኒው እንጀራዋን በልተው ተረከዛቸውን አነሡባት።

የሕማማቱ ወቅት አጭር ቢሆንም ከባድ መሆኑን እናውቃለን። የኮሶ መድኃኒት እንዲያሽር ከተፈለገ በአንድ ጊዜ በከባዱ መወሰድ አለበት። በትንሽ በትንሹ ከተወሰደ አያሽርም። የኢትዮጵያም ሕማማት እንደዚሁ ነው። በፊስካል ፖሊሲ፣ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ነጻነትን በማስተዳደር፣ በክልል አደረጃጀት፣ በሲቪል ሰርቪስ፣ በጋራ ትርክት ግንባታ፣ ወዘተ. የተረከብናቸው ውዝፍ ዕዳዎች ብዙ ናቸው። ወገባችንን አሥረን፣ እጅጌያችንን ሰብስበን መራራውን የኮሶ መድኃኒት ውጠን፣ እነዚህን ችግሮች ካልፈታናቸው ቆመው አይጠብቁንም። በፈጣኑ ዓለም ውስጥ ቀስ ብለን ልንሄድ አንችልም። ተጠንቅቀን ግን ፈጥነን፤ አስበን ግን ዋጋ ከፍለን መጓዝ አለብን። ይሄ ነው ሕማማቱን የሚያሳጥረው።

ኢትዮጵያ ሕማማቱን ለማለፍ የሚያስችል ኃይል አላት። ከዚህ በፊትም ብዙ አልፋለች፣ አሳልፋለች። የማይተዋት አምላክ አላት። የሚወዳት፣ የሚያስብላት ብቻ ሳይሆን የሚሞትላትም አመራር አላት። ዓላማ አይቶ ዋጋ የሚከፍል ሕዝብ አላት። አንጡራ ሀብት አላት። ይሄ የፈጣሪ፣ የአመራሩ፣ የሕዝቡ እና የአንጡራ ሀብቷ አራት ማዕዘናዊ ዐቅም፣ ሕማማቱን ማሳጠርና ማስቻል ብቻ ሳይሆን ቀጥሎ የሚመጣውን ፋሲካ ረዥም እንዲሆን ያደርገዋል።

ብርቱውን ይዘናል - እንበረታለን፤ ኃይል በሚሰጠው እንታመናለን። ንጽሕናንና ለሀገር ያለንን በጎ ራእይ መሠረት አድገን ቆርጠን እንሠራለን። የጥብርያዶስ ሞቅታም ሆነ የፕራይቶሪዮን ግቢ ጩኸት ከመንገዳችን አያቆሙንም። የሆሳዕና ድጋፍም ሆነ የዕለተ ዓርብ ተቃውሞ መንገዳችንን አያስቀይሩንም። የኢትዮጵያን እውነት ብቻ ተከትለን እንገሠግሣለን። በዚህም ሕማማቱን አሳጥረን የኢትዮጵያን የትንሣኤ ጊዜ እናረዝመዋለን።

በድጋሜ መልካም የትንሣኤ በዓል!

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!

ሚያዝያ 26 ቀን 2016 ዓ.ም

ዜና

# ‹‹ የተረከብናቸውን ድሎች ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል››

- ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን
የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ካለፈው ትውልድ የተረከብናቸውን ድሎች ተገቢ ክብር በመስጠት፣ ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር ስሜት እና አንድነት ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ ይጠበቅብናል ሲሉ የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ገለጹ።

ልጅ ዳንኤል ጆቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮ ለ83ኛ ጊዜ የሚከበረው የድል በዓል የኢትዮጵያ አርበኞች ከአምስት ዓመታት ውጊያ በኋላ የኢጣሊያን ወራሪ ጦር ድል በማድረግ በሀገር ጉዳይ የማይደራደሩ እና መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጁ መሆናቸው መልእክት የተላለፈበት ነው።

በዓሉ የድል እንጂ የነፃነት ቀን አይደለም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ የቀድሞ ትውልድ መልካም ሥነምግባር የተላበሰ፣ ሃይማኖት ያለው፣ ስለሀገሩ ታሪክ የሚያውቅና የሚመራመር፣ የጎረቤት ሀገሮችን ሁኔታ የሚገነዘብ እና ሊኖር የሚችለውንም ችግር አውቆ ለሀገር ሰላም መስፈንና አንድነት በተጠንቀቅ የሚቆም ሕዝብ እንደነበር አስታውሰዋል።

ይህንን መልካም ተግባር የአሁኑ ትውልድ ከታሪክ በማንበብና በመስማት የቀድሞ አባቶችና አያቶቹ ሲሰሩ የነበሩትን ታሪክ የሚደግም ሊሆን



እንደሚገባውም አመልክተዋል።

አሁን ያለው ትውልድ በትምህርትም በስራም ታታሪ መሆኑን ያስመሰከረ ነው።ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉትም በንግድ ንቅናቄ ሰፊ እይታ ያላቸው፣ ደፋር መሆናቸውንም የሚያሳዩ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ብለዋል።

የሌሎች ሀገሮችን ቋንቋ አውቀው ከእነርሱ ጋር በንግድ እና በሌሎች የሁለትዮሽ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው።እድሉን እያገኙ ሲሄዱ ከዚህም በላይ እንደሚሰሩ አምናለሁ።ተምረዋል፣ ታሪኩንም ያውቃሉ በተለያየ መልኩ ሥራ ላይ እያዋሉትም ይገኛሉም ነው ያሉት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አብዛኛው ወጣት ትውልድ በመልካም ስብዕና የተቀረፀ ነው።ሆኖም ግን አንዳንዶች ለመልካም ስብእና ተቃራኒ የሆነ ተግባር የሚፈጽሙ የሉም ማለት አይቻልም።በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በመንግሥት ድጋፍ ተሻሽለው ወደ መጥፎ ስብእና የገቡ ወጣቶች ይለወጣሉ። ትውልዱ ሰውን ከሚጎዳ እና አእምሮን ከሚያበላሹ ነገሮች እየተቆጠበ የሚሄድ ከሆነ የተጣለበትን አደራ በማስቀጠል የታሰበበት እና የታለመበት ቦታ ያደርሳል።

በየዓመቱ ሚያዝያ 27 የሚከበረው የድል በዓል በየጊዜው እየደመቀ መከበሩ በሕይወት ላሉት፣ ለሀገር መስዋዕት እሆናለሁ ብሎ ለተሰለፉት የመከላከያ ሠራዊትና የፀጥታ አካላት በሙሉ የሚያስደስት መሆኑን ጠቁመው፤ ለሀገሩ መስዋእት የሆነ ትውልድ በሕይወት ዘመኑ መስዋዕት የሆነለት በዓል ሲከበርለት መመልከት ይፈልጋል፤ ይሄ ለእዛ ትውልድ ሽልማቱም ምስጋናውም ነው ሲሉም አክለዋል።

## ‹‹ከአጭሩ ሕማማት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሰሞነ ሕማማት ሐሰት ያሸነፈች፣ እውነት የተሸነፈች መስላ የታየችበት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብዙዎች መሥዋዕትነትን ፈርተው የሸሹበት ነው። በጽናት የቆሙ ጥቂቶች ግን ከሕማማቱ አልፈው ትንሣዔውን ለመመልከት ችለዋል።

ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ እያለፈች መሆኑን አመላክተው፤ ወቅቱ ለኢትዮጵያ የሕማማት ሰሞን ይሆን ይሆናል። የኢትዮጵያ ሕማማት አጭርና ከባድ ቢሆንም ሕማማቱን ለማለፍ የሚያስችል ኃይል አላት። ከአጭሩ ሕማማት በኋላ ረዥሙ የኢትዮጵያ ትንሣዔ የሚመጣ ይሆናል ብለዋል።

የከተማው ጩኸት እና የሐሰቱ ወሬ እንኳን በሩቅ የነበሩትን፣ ቅርብ የነበሩትንም እንዳሸነፋቸው ጠቅሰው፤ የሆሳዕና ዕለት ደግፈው የወጡት ከሦስት ቀን በኋላ ለተቃውሞ ወጥተዋል። ድጋፋቸውም ተቃውሟቸውም የጥቅም እንጂ የመርሕ አልነበረም።

በዚህም በሌላ ጊዜ ለሞት የሚፈላለጉ አካላት እውነትን ለመስቀል ሲሉ ግን ተባብረው ቆመዋል ብለዋል።

ከሕማማቱ ይልቅ ትንሣዔው ይበልጣል፤ ይረዝማልም። ሕማማቱ አምስት ቀን ሲሆን ትንሣዔው ግን አስር እጥፍ ይሆናል። የአምስት ቀን ፈተና የሃምሳ ቀን ዋጋ አለው።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የሕማማቱን ሽብርና ዋይታ፣ መከራና እንግልት ለተመለከተ ትንሣዔ የሚመጣ አይመስለውም። ትንሣዔው ግን የታመነና የተረጋገጠ ነው። የበለጠ ማረጋገጥ የሚቻለውም ጸንቶ እንደ ዮሐንስ በመቆም ብቻ ነው።

የተነሣነው ኢትዮጵያ እንደምትፈተን አውቀንም፤ አምነንም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ለዘመናት የኖሩ ስብራቶችንና ብልሽቶችን ልናክም ስንነሣ መንገዱ አልጋ በአልጋ አይሆንም። ከችግሩ ማትረፍ የለመዱ አካላት ዝም አይሉም።

በመሆኑም እኛ ልጆቿ መከራውን ተቀብለንና ቀንበሩን ተሸክመንላት ትንሳዔዋ እውን እንዲሆን ልንተጋ ይገባል።

የሕማማቱ ወቅት አጭር ቢሆንም ከባድ መሆኑን እናውቃለን። የኮሶ መድኃኒት እንዲያሽር ከተፈለገ በአንድ ጊዜ በከባዱ መወሰድ አለበት። የኢትዮጵያም ሕማማት እንደዚሁ ነው ብለዋል።

በፊስካል ፖሊሲ፣ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ነጻነትን በማስተዳደር፣ በክልል አደረጃጀት፣ በሲቪል ሰርቪስና በጋራ ትርክት ግንባታ የተረከብናቸው ውዝፍ ዕዳዎች ብዙ ናቸው ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ወገባችንን አስረን፣ እጅጌያችንን ሰብስበን መራራውን የኮሶ መድኃኒት ውጠን፣ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ተጠንቅቀን ግን ፈጥነን፤ አስበን ግን ዋጋ ከፍለን መጓዝ ይጠበቅብናል።

ኢትዮጵያ ሕማማቱን ለማለፍ የማይተዋት አምላክ፣ የሚወዳት፣ የሚያስብላት ብቻ ሳይሆን የሚሞትላትም አመራር፣ ዓላማ አይቶ ዋጋ የሚከፍል ሕዝብ እንዲሁም አንጡራ ሀብቷ ኃይል እንደሚሆናት አመላክተው፤ የፈጣሪ፣ የአመራሩ፣ የሕዝቡ እና የአንጡራ ሀብቷ አራት ማዕዘናዊ አቅም፣ ሕማማቱን ማሳጠርና ማስቻል ብቻ ሳይሆን ቀጥሎ የሚመጣውን ፋሲካ ረዥም እንዲሆን ያደርገዋል።

የጥብርያዶስ ሞቅታም ሆነ የፕራይቶሪዮን ግቢ ጩኸት ከመንገዳችን አያቆሙንም ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ የሆሳዕና ድጋፍም ሆነ የዕለተ ዓርብ ተቃውሞ መንገዳችንን አያስቀይሩንም። የኢትዮጵያን እውነት ብቻ ተከትለን እንገሠግሣለን። በዚህም ሕማማቱን አሳጥረን የኢትዮጵያን የትንሣዔ ጊዜ እናረዝመዋለን ብለዋል።

## በመዲናዋ ባለፉት ዘጠኝ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተገንብተው ለነዋሪዎች ተላልፈዋል ያሉት ከንቲባዋ፤ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ6 ሺህ 700 በላይ ቤቶች ተገንብተዋል ብለዋል።

በዓመቱ መጨረሻ ከእቅድ በላይ ቤቶችን ለመገንባት እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ በቀጣይ ተጨማሪ አካባቢዎችን የመቀየርና ለነዋሪዎች ምቹ የማድረግ ሥራ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

ከተማን ለመቀየር በተሠሩት ሥራዎች ሳይረኩ ብዙ መሥራትን ይጠይቃል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የተጀመሩ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

መንግሥት የጀመራቸው ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ እየቀየረ ነው ያሉት ከንቲባዋ ፤ በከተማ አስተዳደሩ ፕሮጀክትን ጀምሮ መጨረስ ባህል እየዳበረ መምጣቱን ገልጸዋል።

ቤቶቹ ለዘመናዊ አኗኗር አመቺ በሆነ መልክ የተገነቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ቤቶቹ በርካታ ልበቀና ባለሀብቶችን በማስተባበር የተገነቡ ናቸው ብለዋል።

ፈርሰው የተገነቡት ቤቶች ለኑሮ አመቺ ያልነበሩና በአጭር ጊዜ ተመልሰው የተገነቡ መሆናቸውን በመግለጽ፤ በበጎ አድራጎት ተግባሩ የተሳተፉ ባለሀብቶችንም አመስግነዋል።

የተገነቡ ቤቶችን የማስረከብ መርሃግብሩ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የተገኙበትን ጨምሮ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተካሂዷል።

## ምዕመናን በዓሉን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመሆኑም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ኃጢአተኛ ሆኖ ስለተገኘ ቤዛ ሆኖ የሚያድነው ያስፈልገው ነበርና፤ በእግዚአብሔር ፊት ለሱ የሚመጥን ንጹህ አካል ከፍጡራን ወገን አልተገኘምና እሱ ራሱ ሰው ሆኖ የሰው ቤዛ ለመሆን በሥጋ ተገለጠ፣ በዚህም መሠረት የሰው ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ በመሰቀል ንጹህ ደሙን አፈሰሰ፤ በዚህም ምክንያት የሰው ኃጢአት በሥርየት ተዘጋ ብለዋል።

የጌታችንን ትንሣኤ ስናከብር የኛንም ትንሣኤ በማሰብ ሊሆን ይገባል፡፡ የሱ ትንሣኤ ለእኛ ትንሣኤ በኩር፣ ማሳያና ማረጋገጫም መሆኑን ገልጸው፤ እግዚአብሔርም በየዕለቱ የሚፈልገው የኛን ትንሣዔ ማየት ነው፡፡ ትንሣዔያችንም አምነን ስንጠመቅ ተጀምሮ ከመቃብር ስንነሣ የሚጠናቀቅ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እግዚአብሔር ክሕደትን፣ ከሕገ ተፈጥሮ ያፈነገጠ ጸያፍ ተግባርን፣ ጥላቻን፣ ጦርነትን፣ መለያየትን፣ ራስን ብቻ መውደድን፣ መጨካከንን፣ ግብረ ኃጢአትን፣ ፈሪሐ እግዚአብሔር ገንዘብ አለማድረግን፣ ፈጣሪን አለማመንን የተጸየፈ ምእመን ማየት ይፈልጋልና እነዚህንና መሰል መጥፎ ተግባራትን መፈጸም እንደማይገባ አስታውቀዋል፡፡

ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ፣ በፍቅር ፣ በሰላም፣ በይቅርታ ፣ በመከባበር ፣ በአንድነት እንዲሁም በመተሳሰብ ሃይማኖታዊና ግብረ ገባዊነት ጸንተን መኖር ከቻልን ትንሣኤ ማለት እሱ ነው ብለዋል፡፡

በዓለ ትንሣዔ የእግዚብሔር ፍቅር መገለጫና የተስፋችን ማሳያ መሆኑን በመገንዘብ ምእመናን ለተራቡ፣ ለተጠሙ፣ ለታረዙ፣ ለታመሙና ለታሰሩም ሁሉ ካለን አካፍለን በመስጠት ከኛ ጋራ በመንፈስና በሞራል በዓለ ትንሣኤውን እንዲያሳልፉ ልናደርግ ይገባል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ ሱራፌል በበኩላቸው፤ እነሆ የዓለም ንጉሥ ተነስቷልና እንቀበለው፣ እናክብረው፣ እናምስግነው፣ ሁላችንም በትንሳዔው ብርሃን ለሀገራችንና ለሕዝባችን የሰላም መሣሪያዎች እንሁን፡፡ የችግሮቻችን መውጫ ቁልፍ ሰላም ብቻ በመሆናቸው ሰላምና ፍቅርን ጌታ በትንሳዔው እንዲያድለን በጸሎት እንትጋ ሲሉ አስገንዝበዋል።

ምዕመናን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳዔ ሲያከብሩ የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት፣ ተፈናቃዮችን ወደቀድሞ መኖሪያቸው በመመለስ እና ያዘኑትን በማጽናናት መሆን እንዳለበት ገልጸው፤ ለታመሙት ምህረትን፣ ለደከሙት ብርታትን፣ ለታሰሩት ይቅርታ፣ ላዘኑት መጽናናት፣ በጭንቀትና በመከራ ላይ ለሚገኙ ሰላምና ፍቅሩን እንዲሰጣቸው ምዕመኑ በጸሎት እንትጋ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻድቁ አብዶ እንደገለጹት፤ የትንሳኤ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን የተጓዘበትን የትህትና መንገድ፣ የመከራና የሥቃይ ጎዳና እንዲሁም ስለመተላለፋችን የከፈለልንን የሕይወት መስዋዕትነት በማሰብ መሆን አለበት፡፡ እንደ ፓስተር ጻድቁ ገለጻ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር በጭካኔ ላይ ብርቱ እንደሆነና የክህደት ጎርፍ ፍቅርን ሊጠርግ እንደማይችል አስረድቶናል፡፡ ከዚህም ፍቅር የዘር ግንድ የማይቆጥር፣ የብሔር ድንበር የማያግደው፣ ጥላቻን ማሸነፊያ፣ የበቀል ፍላጎትን ማስወገጃና ሰላምን ማስፈኛ መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ምዕመናን በዓሉን ሲያከብሩ አቅም የሌላቸውን ወገኖች በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸው፤ በዓሉ የደስታ፣ የፍስሃና የትንሣዔውን እውነት የምናስተውልበት ይሁንልን ሲሉ መልክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ ባስተላለፉት የበዓል መልዕክታቸውም፤ የትንሳዔ ወቅት ማንነታችንን የሚያስገነዝበን የሰላም ሰዎች መሆናችንንም የሚያስታውሰን ወቅት በመሆኑ የሰላም ሰዎች ሰላምን ተግተው የሚሹና በባለ አደራነት መንፈስ ሌሎችን ለመታደግ የሚተጉ ናቸው ብለዋል፡፡

ጌታችን ለተሳደቡት፤ ለዘበቱበት፤ ላስጨነቁትና ላዋረዱት የአጸፋ ምላሽ አልሰጠም፤ ይልቅስ በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳን የተናገረው የእርቅና የሰላም ቃል የመስቀል ስቃይ እንከኳን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅ አገልግሎቱን ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ምዕመናን ሰላምን በሰላም መንገድ ብቻ እንሻት፤ መሻት ብቻ ሳይሆን ዋጋ ቢያስከፍልም እንኳን ዋጋ ለመክፈል እንፍቀድ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የክርስቶስን መንገድ በመምረጥ መልካሙን ተግተን በመፈለግ የዘንድሮው የትንሳዔ በዓል ተስፋን እንዲሰንቅልን በጸሎት እንትጋ ብለዋል፡፡

የሃይማኖት አባቶቹ በዓሉ የሰላም፣ የደስታ፣ የፍቅርና የመተሳሰብ እንዲሆን የተመኙ ሲሆን፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስን የትንሳዔ በዓል ሲያከበር በመረዳዳትና በመተጋገዝ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የኮሪደር ልማቱ እና አዲስ የሥራ ባህል

**እስማኤል አረቦ**

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትፈተንባቸው ከቆየችባቸው የልማት ማነቆዎች ውስጥ የፕሮጀክቶች መጓተት አንዱና ዋነኛው ነው። ሀገሪቱ በፕሮጀክቶች መጓተት የምትታወቅና በርካታ የሕዝብ ሀብትም ለኪሳራ ሲዳረግባት የቆየች ሀገር ነች።

ይህ ደግሞ ከዝቅተኛ የስራ ባህልና ከፕሮጀክቶች የሥራ አመራር ክህሎት ማጣት ጋር የሚያያዝ ነው። በዋነኝነት የሥራ ባህላችን ዝቅተኛ መሆን የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ዓመታት እንዲፈጁና እንደሀገር የኢኮኖሚ ኪሳራ እንዲደርስብን ምክንያት ሆኗል። በተለይም ከመሠረተ ልማት ግንባታ ጋር በተያያዘ ብዙ መገለጫዎች ያሉት ነው። በደካማ የሥራ ባህልና በፕሮጀክቶች የአመራር ጥበብ ማነስ የተነሳ ተጀምረው የተጓተቱና ጭራሹንም መጨረስ ያልቻልናቸው ፕሮጀክቶች ተቆጥረው የሚያልቁ አይደሉም።

ተጀምረው ከተረሱት ውስጥ የስኳር ፋብሪካዎች፤ የማዳበርያ ፋብሪካ፤ የግብርና ማቀነባበሪያዎችና የመሳሰሉት እስካሁንም ተጀምረው የቀሩ ናቸው። በደካማ የሥራ ባህል የተነሳ በጾም በጸሎት የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን ስናይ ደግሞ እንደሀገር የት እንደነበርን በቀላሉ መገንዘብ ያስችለናል። አብነት እንዲሆነን ጥቂቶቹን እንመልከት።

ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ባለ 12 ወለል ህንጻ ለማጠናቀቅ እስከ 15 ዓመታ ይወስድ እንደነበረ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ። ለአብነት መሃል ፒያሳ ላይ የሚገኘው በተለምዶ አራዳ ህንጻ ተብሎ የሚታወቀው ባለ 12 ወለል ህንጻ ከ15 ዓመታት በላይ ወስዷል። በደርግ ጊዜ ተጀምሮ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የተጠናቀቀ ዓመታትን የፈጀ ህንጻ ነው።

የመንገድ ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ አንዱ መገለጫቸው ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ መፍጀታቸው ነው። ለአብነትም ከአቡነ ጴጥሮስ እስከ አስኮ ያለው መንገድ በሁለት ዓመታት ውስጥ ይጠናቃል ተብሎ ከአምስት ዓመታት በላይ መውሰዱ የሚታወቅ ነው።

በተመሳሳይም የኮተቤ አራራት መንገድ በግንባታ መዘግየት ብዙዎችን ሲያማርር ቆይቷል። መንገዱ በሁለት ዓመታት ውስጥ ይጠናቃቃል ቢባልም ከሰባት ዓመታት በላይ በመዘግየቱ መንግሥትን ለበርካታ ወጪ ህብረተሰቡን ደግሞ ለቅሬታ ዳርጓል።

በተጨማሪም በ2009ዓ.ም የተጀመረውም የቃሊቲ ማሳለጫ በሁለት አመት ተኩል ይጠናቀቃል ቢባልም አምስት አመታትን ወስዷል።

ከመንገድ ፕሮጀክቶች ወጣ ስንልም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመማርያና አስተዳደር ህንጻዎች በርካታ አመታትን በመፍጀት በፕሮጀክት መዘግየት የሚጠቀሱ ናቸው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚካሄዱ ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመጠናቀቃቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥላ ከማጥላታቸውም በላይ ዩኒቨርሲቲውን ለተጨማሪ ወጪ የዳረጉ ናቸው።

ሌላው በግንባታ መዘግየት ተጠቃሽ የሆነው የጳውሎስ ሆስፒታል ማስፋፍያ ግንባታ ነው። ይህ ማስፋፍያ ግንባታ ከተጀመረ 10 ዓመታትን ሊያስቆጥር ጥቂት ጊዜያት ብቻ ይቀራሉ። የግንባታው መጓተትም ሆስፒታሉ ያለበትን የህክምና መስጫ ክፍሎች እጥረት ከማባባሱም ባሻገር ሆስፒታሉን ከፍተኛ ለሆነ ወጪ መዳረጉን የተወካዮች ምክር ቤት የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ማንሳቱ የሚታወስ ነው።

ግዙፉ የዓባይ ግድብም የፕሮጀክት መጓተት ሰለባ ከሆኑ ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነቱ የሚነሳ ነው። የዓባይ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ በአምስት አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም 13 አመታትን አስቆጥሯል።

የዓባይ ግድብ በ 82 ቢሊዮን ብር ወጪ ለመገንባት ውል ቢገባም በነበረው እጅግ ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር ግድቡ ከመጓተትም አልፎ የህልውና አደጋ ገጥሞት ቆይቷል። ግድቡን ከገጠመው መሰናከልና

> ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ባለ 12 ወለል ህንጻ ለማጠናቀቅ እስከ 15 ዓመታ ይወስድ እንደነበረ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ለአብነት መሃል ፒያሳ ላይ የሚገኘው በተለምዶ አራዳ ህንጻ ተብሎ የሚታወቀው ባለ 12 ወለል ህንጻ ከ15 ዓመታት በላይ ወስዷል፡፡ በደርግ ጊዜ ተጀምሮ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የተጠናቀቀ ዓመታትን የፈጀ ህንጻ ነው

የሞት አደጋ ለማዳን በርካታ ጥረቶች ተደርገው አሁን ከ95 በመቶ በላይ ማድረስ ተችሏል። ሆኖም ቀደም ሲል በተከሰተው የግንባታ መጓተት የግድቡ ግንባታ ከ13 ዓመት በላይ ከመውሰዱም በሻገር የግንባታ ወጪውን ከሶስት እጥፍ በላይ አሳድጎታል።

የኮይሻ ግድብም ቢሆን በአምስት አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ግንባታው ቢጀመርም ዘንድሮ ስምንተኛ አመቱን ይዟል። ግድቡ በነበረበት ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረትና ቀውስ ለወራት ቆሞ የነበረ ሲሆን ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ችግሩ ከመሰረቱ እንዲስተካከል በመደረጉ ግንባታው በመፋጠን ላይ ይገኛል።

እንደ አጠቃላይ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከለውጡ በፊት በነበረው ብልሹ አሰራር ምክንያት በኢትዮጵያ የተለያዩ 102 ፕሮጀክቶች መጓተታቸው ምክንያትም 42 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ ጠይቀዋል።

የፕሮጀክቶች መጓተት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጉዳቶች ያሉት ሲሆን ፕሮጀክቶቹ ከተመደበላቸው በጀት ተጨማሪ ወጪ ይጠይቃሉ፤ በብድር የሚሰሩ ከሆነ ተጨማሪ ወለድ እንዲከፈል ያስገድዳሉ፤ ሌላ ብድር ለማግኘትም መሰናከል ይፈጥራሉ። ፕሮጀክቶቹ በወቅቱ ተጠናቀው ይሰጡት የነበረውን ጥቅምም ያሳጣሉ ።

ቀደም ሲል በነበረው አሰራር አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የሚዘገዩት በደካማ የስራ ባህል ምክንያት፤ በመንግሥታዊ ውስብስብ ቢሮክራሲያዊ አሰራር፣ቀና ትብብር አለመኖር፣ በፕሮጀክት አስተዳደር ችግርና በዕቅዶች የተፈጻሚነት ጉድለት መሆኑ በጥናት ከተረጋገጠ በኋላ በኢትዮጵያ አዲስ የፕሮጀክት አፈጻጸም መመዝገብ ጀምሯል። አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶችም አስገራሚ በሆነ ፍጥነት ተጠናቀው ለአገልግሎት ሲበቁ መታየታቸው ሀገሪቱ በፕሮጀክቶች መጓተት ስትከፍል የነበረው ኪሳራ ከፍተኛ እንደነበር ለመገንዘብ ያስችላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጓተቱትም ሆነ አዲስ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ረገድ ብዙ መሻሻሎች ታይተዋል። የግንባታ ሂደት በሪፖርት ብቻ ሳይሆን በቦታው በመገኘትም ጭምር ያሉባቸውን ተጨባጭ ችግሮች እንዲቀረፉ በማድረግ እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችም በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ በማድረግ ረገድ አዲስ የፕሮጀክት አጨራረስ ምዕራፍ ላይ መድረስ ተችሏል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር ከመጣ ወዲህ ለዘመናት ሲጓተቱ የነበሩ ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለአገልግሎት ከማብቃት ባሻገር የተጀመሩትን በፍጥነት የማስቀጠልና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በሚገርም ፍጥነት ለውጤት ማብቃት ተችሏል። ከዓመታት በፊት ተጀምረው በመጓተት ብሎም በመክሰም ሂደት ውስጥ የነበሩትን የዓባይ እና የኮይሻ ግድቦችን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተችሏል። የንግድ ባንክን ህንጻ ከመቆም ታድጎ ለአገልግሎት በቅቷል። የሀገር መከላከያ ሰራዊት እና የኢንሳ መስርያ ቤቶች አምረውና ደምቀው ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል።

በገበታ ለሀገር ከተገነቡት ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ማዕከል ነው። ይህ ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተጠናቀቁና ኢትዮጵያ ያላትን ፕሮጀክት አፈጻጸም ታሪክ ከፍ ያደረገ ትልቅ ፕሮጀክት ነው።

አዲሱ አመራር ነባር ፕሮጀክቶችን ከማጠናቀቅ አልፎ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በመጨረሽ የብዙዎችን ይሁንታ አግኝቷል። ከእነዚህ ውስጥ ገበታ ለሀገር ተብለው ከተጀመሩና ለመዲናዋ መስህብ ከሆኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ የአንድነት፤ የወዳጅነትና የእንጦጦ ፓርኮች ተጠናቀው የአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋል። የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክትም የከተማዋ አንዱ ድምቀት ለመሆን በቅቷል።

በአይነቱ ለኢትዮጵያ የመጀመርያ የሆነውም የሳይንስ ሙዚየምም በአጭር ጊዜ ተገንብቶ የከተማው መስህብ ሆኗል። አሁን ደግሞ ሙሽራዋ አዲስ አበባ በአዳዲስ ፕሮጀክቶች ብቅ ብላለች። አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ እንቅስቃሴ መናኸሪያ እንደ መሆኗ ይህን የሚመጥን ልማት እየተከወነላት ይገኛል። የልማቱ መጠርያም የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ይሰኛል ።

በፍጥነትና ጥራት እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት ስራዎች እጅን አፍ ላይ ለመጫን የሚያስገድዱ ናቸው።

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች መሆናቸው ታውቋል። ስራውም በስድስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅም ተነግሯል።

በአጠቃላይ በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሰረቱ የሚቀይር ነው። ከሁሉም የሚያስደስተው ደግሞ ስራውን በታያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚደረገው ርብርብ እና ጠንካራ የስራ ባህል አግራሞትን የሚፈጥር መሆኑ ነው።

አጠቃላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለተመለከተ የኮሪደር ልማቱ በታሰበለት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መገመት አያዳግትም። የተሽከርካሪ መሄጃ አስፋልቱን እና የእግረኛ መንገዱን ስፋት ለተመለከተውም ዓለም አቀፍ ደረጃን ባሟላ መልኩ እየተገነባ መሆኑን ያመላክታል።

የኮሪደር ልማቱን ተዘዋውሮ ለመመልከት እድል ላገኘ ሰው የሚያስገርመው ነገር የሰራተኞች የስራ ትጋትና ቅልጥፍና ነው። በዚህ ሁሉ ትጋት ውስጥ ደግሞ ስራው ጥራቱን ጠብቆ መሄዱ የሚያስገርም ነው። የተለያዩ የግንባታ ማሽነሪዎች ሲርመሰመሱ፤ሰራተኞች ደፋ ቀና ሲሉ ፤ከፍተኛ አመራሮች አቧራና ጸሃይ ፤ጨለማና ብርድ ሳይበግራቸው ክትትል ሲያደርጉ ለተመለከተ በሀገራችን አዲስ የስራ ባህል እየተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ አያዳግተውም።

ለአብነት ከዓድዋ ሙዚየም እስከ መገናኛ ያለውን መንገድ ብንመለከት ነዋሪዎቹን አሳምኖ ከማንሳትና ቤቶቹን አፍርሶ ለግንባታ ክፍት እስከ ማድረግ የወሰደው ጊዜ ከሁለት ሳምንታት የሚበልጥ አልነበረም። በተለይም ለመንገድና ለሌሎች መሰረተ ልማቶች ግንባታ አመቺ ያልሆኑ ቦታዎችን በፍጥነት አጽድቶ ምቹ ለማድረግና ወደ ግንባታ ለመግባትም የወሰደው ጊዜ በጣት ከሚቆጠሩ ቀናት የዘለለ አይደለም። ከዚህ ቀደም በነበሩ ጊዜያት ነዋሪዎችን አሳምኖ ወደ ተዘገጀላቸው ምትክ ቦታ ለማዘዋወርና ወደ ግንባታ ለመግባት አመታትን ይወስድ እንደነበረ በግልጽ የሚታወቅ ነው።

ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ ግዙፍ ስራዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ ተጠናቀው የአስፋልት ማንጠፍ ስራ፤ የእግረኛ መንገድ ንጣፍ፤ የመንገድ ጠርዞችን የማስዋብና የማሳማር ስራዎች እጅግ በፈጠነ መልኩ ሲከናወኑ ማየት የሚያስገርም ነው።

መሸቶ በነጋ ቁጥር ተጀምረው የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን የተመለከተ በፕሮጀክቶች መጓተት ሀገሪቱ ምን ያህል ወደኋላ እንደተጎተተች ለመረዳት አያዳግተውም። በፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት ቀደም ሲል ተጀምረው ከንቱ የቀሩት የያዩ ማዳበርያ፣ የስኳር ፋብሪካዎች፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ በየቦታ እንደ አሸን ተጥለው የሚገኙ የግንባታ ማስጀመርያ የመሰረት ድንጋዮች ይህችን ሀገር በብዙ ዋጋ እንድትከፍል ያደረጓት ናቸው።

እነዚህ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ገንዘብ የባከኑባቸው ከመሆኑም ባሻገር በከፍተኛ መጠን ባለው ወለድ በተገኘ የውጭ ብድር የተጀመሩ በመሆናቸው ሀገሪቱን እስካሁን ከፍላ ላልጨረሰችው ዕዳ ዳርጓታል። ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ተረት ሆነው ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማጠናቃቅ ባህል እየሆነ መጥቷል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ዓመት በዓልን ከድምፅ አልባዎቹ ልጆቿ ጋር

**አስመረት ብስራት**



ለዓይን የምታሳሳ ልጅ ናት። ከአፏ የሚወጡ የተቆራረጡ ድምፆች እንጂ ትርጉም ያለው ቃል መናገር አትችልም። ፀጉሯ መልኳ፤ ካላት የእንቅስቃሴ ችግር ጋር ተደምሮ ውስጥን የሚሰረስር የማዘን ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል። ይህች ቆንጆ ልጅ ሰሟ ሄለን ይባላል። ሄለን በማህበሩ ውስጥ ከሚኖሩት ተደራራቢ የጤና ችግር ካለባቸው ልጆች መካከል አንዷ ናት። የሄለን ለየት ያለ ባህሪዋ አሳዳጊዎቿ ከሌሎች ህጻናት ቀድመው ሂሉዬ የኔ ቆንጆ ብለው ሰላም ካላልዋት ታለቅሳለች። አሳዳጊያቸው ሲስተር አሳየች ይርጋ ከዚህ ባህሪዋ የተነሳ ቀኑብሽ የሚል ቅፅል ስም ሰጥታታለች።

በተጨማሪ ሄለንን ጨምሮ ሁሉም ልጆች እናታቸውን ሲስተር አሳየችን በሽታ ይለይዋታል/ ያውቋታል። እናም ሄለን ሲስተር አሳየች ወደ አጠገቧ ከቀረበች ልብሷን መያዝ፤ በጣም እቅፍ አድርጋ መያዝ ትወዳለች። ይህ ታድያ የሚያሳየው አንድ እናት አርግዛና ወልዳ ከምታገኘው የወላጅነት ፍቅር በተጨማሪ ላልወለደችው፣ የስጋ ትስስር ከሌላት ልጅ ጋር በከባድ ሁኔታ መተሳሰር እንደሚቻል የሚያሳይ አስደናቂ የፈጣሪ ጥበብ ነው።

ሄለን አትናገርም፣ አትሰማም፣ አትሄድም፣ ተደራራቢ የጤና ችግሮች አሉባት። ይህ ሁሉ ቢሆንም ቅሉ እናቷ ማን እንደሆነች ማወቋና የወላጅነትና የልጅነት ትስስርና ቁርኝት ማግኘቷ በጣም ልብ የሚነካና ሰውኛ ስሜት የሚፈጥር ነው። ለማንም ሰው ቢሆን ተደራረቢ የጤና ችግር ያለው አንድ ልጅን ለመያዝ በሚቸገርበት በዚህ ዘመን ንፁህ የእናትነት ፍቅር እየሰጠች በርካታ ልጆችን የምታሳድገው ሴት፤ ካልወለደቻቸው ልጆች ጋር እውነተኛ እናታዊ ቁርኝት ካላት ሴት ጋር ቆይታ አድርገናል።

በርካታ ሞግዚቶች፤ ፅዳት ሰራተኞች የሞሉበት በፅዳት የተያዙት ክፍሎች ለዓይን ይስባሉ። ልጆቹ በራሳቸው ማድረግ የሚችሉት ነገር ባለመኖሩ ሁሉም የሰውን ድጋፍ ይሻሉ። ሙሉ ለሙሉ ንፅህናቸው ተጠብቆ በልተው ጠጥተው፤ ደህንነታቸው ተጠብቆ መዋል ማደራቸውን እናታቸው ሲስተር አሳየች ትከታተላለች። የእነዚህ ልጆች እናት፤ ሌሎች እናታቸው ጋር ሆነው ለሚታገዙ ከሁለት መቶ ሃምሳ በላይ ወላጆች ቀኝ እጅ የሆነችውን ሲስተር አሳየች ይርጋ ለዛሬው የህይወት እንግዳ አድርገን አቅርበናታል።

### ከውልደት እስከ ትምህርት ቤት

ሲስተር አሳየች ይርጋ ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ነው። ከወይዘሮ አለምነሽ ካሴና ከአቶ ይርጋ ተክለማርያም በርካታ ልጆች መካከል አንዷ የሆነችው ሲስተር አሳየች የሕፃንነት ዘመኗ አልቆ እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ አቃቂ በሚገኘው በሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ትምህርት ቤት ገብታ ተማረች።

ከልጅነቷ ጀምራ የእግዚአብሔርን ቃል አውቃና አጥንታ ያደገችው ሲስተር አሳየች ፤ መልካምነት ከነፍሷ ጋር አብሮ እንዳደገ ትናገራለች። በትምህርት ቤታቸው ለየት ያለ መመሪያ እንደነበረና መመሪያው ከልቧ እንደማይጠፋ ትናገራለች። መመሪያውም ልብን አእምሮንና እጅን በሶስት መአዘን ቅርፅ አስተሳስሮ መስራት እንደሚገባ የሚናገር መሆኑን ታስረዳለች። ያ ማለት በጎ ማድረግን፤ ቅንነትንና መታዘዝን፤ ለእግዚአብሔርን መታዘዘን ጨምሮ መልካም ስነ ምግባርን መመሪያ አድርጎ የመኖር ሃሳብ ያለው ነው። እነዚህን ሶስት ነገሮች ከተቀናጁ ለማህበረሰቡ፤ ለሀገርና ለራስ ለወገን በጎ ነገርን ማበርከት የሚችል ትውልድ የሚኖር መሆን ትናገራለች።

በልጅነቷ መዝሙሮችን፤ መንፈሳዊ ድራማዎችና ግጥሞችን እየፃፈች ማቅረብ የምትወድ ልጅ እንደነበረች ትናገራለች። ልጅነቷንና የአፍላ ወጣትነት ጊዜዋን በመልካም ቤተሰብና ትምህርት ቤት መልካምነትን እየተማረች ያደገችው ልጅ በወቅቱ ከፍተኛ ወጤት በማምጣት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባች። ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃን ማጠቃለያ ፈተና ወስዶ ሶስት ነጥብ ማምጣት በጣም ትልቅ ውጤት እንደነበረ የምትናገረው ሲስተሯ፤ በወጤቷ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መግባት ቻለች። በውጤቷ ዩኒቨርሲቲ መግባት ብትችልም እሷ ግን የልጅነት ህልሟ ነርስ መሆን ስለነበር ከፍቷት የነበረ መሆኑን ታስታውሳለች።

በወቅቱ ነርሲንግ ኮርስ ይሰጥ የነበረው ጎንደር ብቻ ስለነበር ቤተሰቦቿ ከእነሱ ርቃ መሄድ እንደማትችል ነግረው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተመደበችበት መማር ጀመረች። የመጀመሪያው አመት ትምህርት አልቆ ሁለተኛው ሲመጣ የታሪክ ትምህርት ክፍል ተመደበች። ታሪክ ጭራሽ ከእርሷ ህልም ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ዝም ብላ ሌሎች አማራጮችን መመልከት ጀመረች። በልጅነቷ የምታያቸው ፊልሞች ላይ የካቶሊክ ሲስተሮች በጦር የተጎዱ ሰዎችን ሲያክሙ፤ በተለያየ ሁኔታ ያሉ ህሙማንን ሲረዱ መመልከቷ እንደእነርሱ መልበስ መናገር በአጠቃላይ እንደእነርሱ የመሆን ፈላጎት እንዳሳደረባት የምትናገረው ሲስተር አሳየች፤ በሙያ ሰውን ረድቶ የማዳን ህልሟን የሚተካ ምንም አይነት የትምህትት ክፍል አላገኘችም ነበር።

ያንን ነጭ ልብስ ለብሶ ከማገልገል የበለጠ ምንም ነገር የማይታያት ወጣት የመመዝገቢያ ቀን እንዳያልፍባት ታሪክ ዲፓርትመንት ብትመዘገብም አሁንም ግን ህልሟን የምተሳካበት የልቧ የሚሞላበት አማራጭ ማየት አላቆመችም ነበር። ፈጣሪም ህልሟን ኑሪ ሲላት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነርስ እንደሚፈልግ የሰማች አብሮ አደግ ጓደኛዋ ትነግራታለች። በወቅቱ አምጡ የተባሉትን የትምህርት ማስረጃ በሙሉ ይዘው የቀረቡት ሲስተር አሳየችና ጓደኞቿ ከተመዘገቡት አምስት መቶ ሰዎች መካከል ተወዳድረው ያለፉት ስምንት ሰዎች መካከል ሆኑ። ከዛም አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የነርስነት ትምህርቷን ተማረች። በወቅቱ ነርስ መሆን የነፍሷ ጥሪ የነበረው ወጣት በጥሩ ውጤት ትመህርቷን አጠናቀቀች። በመቀጠል በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚሰራው ትኩረት ለሴቶችና ለህፃናት የሚል ተቋም ካቋቋመች በኋላ በሶሺዮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝታ ሶሺዮሎጂስት ለመሆን በቃች።

### ከአባት ወደ ልጅ የታሳለፈ ደግነት

በርካታ ልጆች ያደጉበት ቤት ውስጥ ያደገችው ሲስተር ገነት አባቷ በልጅነቷ ያደርጉት የነበረውን የበጎነት ስራ መቼም እንደማትረሳው ትናገራለች። በልጅነታቸው አባት ለለቅሶም ሆነ ለተለያዩ ጉዳዮች ገጠር ደረሰው ሲመለሱ አሳዳጊና ረዳት የሌላቸውን ልጆች ይዘው ይመጡ እንደነበር ታስታውሳለች። ከአንድ እናትና አባት የተወለዱ ልጆች አስር ቢሆኑም አባታቸው በየጊዜው ይዘዋቸው የሚመጡ ልጆች ተጨምረው የቤተሰቡ ቁጥር ወደ ሃያ ሁለት ደርሶ፤ ከእነርሱ መሃል ሆና ማደጓን ትናገራለች። ቤት ውስጥ የሚያግዙ ሰዎች ፤ አባቷ የነበራቸው የእህል በረንዳ ንግድ ላይ የሚሰሩ ሰዎች ሲጨማመሩ ሰፊ ቤተሰብ አብሮ መኖሩ እና በጋራ ማደግ የተለያዩ ትርፎች እንደነበሩት ታብራራለች።

> ከልጅነቷ ጀምራ የእግዚአብሔርን ቃል አውቃና አጥንታ ያደገችው ሲስተር አሳየች፤ መልካምነት ከነፍሷ ጋር አብሮ እንዳደገ ትናገራለች

ቤታቸው ውስጥ የሚኖሩ ልጆችም ሆኑ ቤት ውስጥ የተወለዱት በእኩልነት በመተጋገዝ መንፈስ ማደጋቸው፤ አንዱ ባለቤት አንዱ የጥገኝነት ስሜትን የያዘ አለመሆኑ ሁሉም ልዶች በፍቅር አድገው ለቁም ነገር እንዲበቁ እንዳደረገላቸው ትናገራለች። በዓል ሲሆን አባታቸው በሬ አርደው ለተቸገሩ ሰዎች ቅርጫ ያከፋፍሉ እንደነበር የምታስረዳው ሲስተር፤ በበዓል በር ላይ መጥተው ከሚወስዱ ሰዎች በተጨማሪ አቅም ለሌላቸው ሰዎች ቤታቸው ድረስ በማድረስ መርዳትን ደግነትን ስትለማመድ ማደጓን ትናገራለች።

በእንግድነት ከገጠር የሚመጡትን ሰዎች እግር ማጠብ፤ ምግብ ማቅረብ፤ መኝታን ማዘጋጀት የመሳሰሉ ሰዎችን የመንከባከብ ልምምዶችን ስታደርግ ያደገችው ሲስተር፤ እሷም ሰዎችን መርዳት ህልሟ ሆኖ እስኪሳካ ድረስ መትጋቷን ትናገራለች። ቤት ውስጥ ያለውን ሙያ ጥንቅቅ አድርጎ ከመማር አንስቶ እህል በረንዳ ላይ ያለውን የንግድ ስራ ማገዝ ፤ በትምህርት መጎበዝ ባለው ሰአት ሁሉ መጣጣርና መልፋት ልምምድ ስታደርግ ማደጓን ተናገራለች።

በየእለቱ የሚሰሩ የእህሉን ሂሳብ ተቀብሎ መስራትን፤ እያንዳንዱን እንቅፋት በጥንካሬ ማለፍን፤ ኃላፊነት መሸከምን ፤ ከልጅነቷ ጀምራ ስትለማመድ ቆይታ የሰላች የጠነከረች ባለደግ ልብ ሴት ለመሆን በቃች። ከአባቷ የተማረችውን ደግነት፤ በነርስነት ሙያ ውስጥ የተለማመደችውን ርህራሄ በአንድ አቀናጅታ ለሰው መኖርን ደግነትን የምትሰራበት ተቋም ለመመስረት ስታልም የኖረችው ሲስተር የዛሬ አስራ ሰባት አመት ህልሟን እውን ማድረግ ቻለች።

### ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር ምስረታ

ርህራሄ መገለጫዋ የሆነው ሲስተር አሳየች ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር በይፋ ከመመስረቱ በፊት በኤችአይቪ/ኤድስ እና በሌሎች ምክንያቶች ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት እጆቿን መዘርጋት ጀመረች። የምትኖረው ትንሽ ቤት ተከራይታ ቢሆንም ቤቷ ውስጥ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

**ማህበራዊ**

# የሕይወት ገጽታ

# ዓመት በዓልን...

**ከ7ኛ ገጽ የዞረ**

ጥቂት ልጆችን ለማምጣት ቆርጣ በመነሳት ከምታገኘው ትንሽ ገቢ እያካፈለች ህይወታቸውን ለማስቀጠል መታገል ጀመረች። በእራሷ ጥረት ባላት ትንሽ ገቢ ለመደገፍ የምትሞክራቸው ልጆች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ መጣ።

ከሰው ለምና ተበድራ የእለት ጉርሳቸውን ልታቃምስ ብትሞክርም ብዙ ሕፃናት ወደ ተከራየችበት ቤት በመምጣታቸው የተነሳ የቤቱ ባለቤት ቤት እንድትለቅ ነገሯት። ደርሳ ነክታ የማትጨርሰውን ችግር እንደነካካች የተረዳችው፤ ሲስተሯ እንደዚህ አይነት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች አላማዬ ብላ ከተነሳችበት ህልም ሊያስቀራት እንዳይችል መታገል ጀመረች። መቸገር ከሩጫዋ ሳያቆማት ጥንካሬ ሆኗት፤ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ሆነች ። በዚህ ነው እንግዲህ የሕፃናት እና ሴቶችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የጤና ሁኔታን ለማሻሻል የሚሰራ ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር ከአስራ ሰባት አመታት በፊት አንድ ብሎ የተመሰረተው።

በማህበሩ ያለመችውን ለማሳካት እየታተረች የምትገኘው ሲስተር አሳየች በርካቶች በጥረቷ ህልሟ የተሳካላት ሴት ቢሏትም፣ እስካሁን ያለመችው ህልም ጋር ልትደርስ ባለመቻሏ አልረካችም። በማህበሩ ውስጥ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተጨማሪ ልጆች መርዳት ትፈልጋለች። ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ልዩ የሆነ ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማዕከል ሠርታለች። ይህ ማእከልም የግራር መንደር ተብሎ ይጠራል። በኢትዮጵያ በዓይነቱ የመጀመሪያ ነው።

ሲስተር አሳየች በገንዘብ ነክ ፈተናዎች ወቅት፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት እና ፕሮጀክቱን ለመደገፍ የራሷን ቤት ለመሸጥ ተገድዳለች። ሲስተር አሳየች አካል ጉዳተኛ ሕፃናትን እና የተቸገሩ ሴቶችን በመርዳት የራስ ነፍሷን የምታስደስተው ይህች ሴት ባለትዳርና የሶስት ወንድ ልጆች እናት ነች። ሲስተሯ ከ17 ሺ በላይ ሴቶችንና ሕፃናትን የሰው ፊት እንደ እሳት እየገረፋት ስትረዳና ስትደግፍ ቆይታለች። ይቺ ልበ ብርቱ ሴት በአንድ ማዕከል ውስጥ እያኖረች የእናትነትና የቤተሰብ ፍቅርን እየሰጠች የምታሳድጋቸው ወላጅ እና አሳዳጊ ተንከባካቢ ያልነበራቸው በርካታ ሕፃናቶችም አሏት።

ሲስተር አሳየች ሕፃናቶችን የምታኖራቸው የግለሰብ ቤት ተከራይታ ከፍተኛ ገንዘብ እየከፈለች ስታኖራቸው የቆየች ቢሆንም፤ አሁን ግን መንግሥት ጋርመንት ግራር ሰፈር አካባቢ በሰጣት ቦታ ላይ አጋዥ አካላትን በማፈላለግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሕፃናት ምቹ እና ማራኪ የሆነ ዘመናዊ ቅንጡ ለአካባቢውም እጅግ ማራኪና ሳቢ የሆነ ባለሁለት ፎቅ የሆነውን አኬዢያ ቪሌጅን በአጭር ጊዜ ውስጥ ገንብታ 538 የሚደርሱ ሕፃናቶችን እናቶችን የተሻለ ኑሮ እያኖረች እና እየተንከባከበች ትገኛለች።

ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙትን ወላጅ የሌላቸውን ለችግር የተጋለጡ ሕፃናትን እንዲሁም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ሴቶችን እንዲሁም ተደራራቢ የጤና ችግር ማለትም የአእምሮ እድገት ውስንነት፣ አካላዊና አእምሮአዊ እድገት ውስንነት፣የዓይን ብርሃን ማጣት፣ የመስማት ችግር፣ ሙሉ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሕፃናትና እናቶቻቸውን ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ህይወታቸው እንዲለወጥ ማስቻልን አላማ አንግቦ የሚንቀሳቀስ ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

ሲስተር አሳየች በሀገራችን ካሉ በጎ አድራጊ ባለ ቅን ልቦች መካከል አንዷና ብዙ ያልተዘመረላት ደግ ሴት ነች። ትኩረት ለሴቶችና ሕፃናት የተሰኘ በጎ አድራጎት ድርጅት መሥርታ ለ17 አመታት ያህል ጥቃት በሚደርስባቸው ሴቶች እና ተደራራቢ የጤና እክል ያለባቸው ሕፃናት ላይ ትኩረቷን አድርጋ እየሰራች ሲሆን፤ ይህንኑ የበጎ አድራጎት ስራ በስፋት ለመቀጠል አቅዳ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች።

## የነገ ህልም

ይህቺ ልበ ቅን ድምጿን አጥፍታ ትልቅ ስራ እየሰራች ያለች መልካም ሴት አሁንም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ሁለተኛ የሆነውን ባለዘጠኝ ፎቅ አኬዢያን ህንጻ ለመገንባት እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች።

በመሬቱ ላይ ያሉ ሕንፃዎች መገንባት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ትምህርት ቤቶች፤ ሆስፒታሎች፤ ሙአለ ሕፃናት፤ ፊዚዮ ቴራፒ



**ቤታቸው ውስጥ የሚኖሩ ልጆችም ሆኑ ቤት ውስጥ የተወለዱት በእኩልነት በመተጋገዝ መንፈስ ማደጋቸው፤ አንዱ ባለቤት አንዱ የጥገኝነት ስሜትን የያዘ አለመሆኑ ሁሉም ልጆች በፍቅር አድገው ለቁም ነገር እንዲበቁ እንዳደረገላቸው ትናገራለች**

አገልግሎቶች የሚሰጥበት ማእከል፤ የአመጋገብ እና የመዝናኛ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ይህም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት አካላዊ፣ ቁሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ ትምህርታዊ እና የጤና ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት የኑሮ ሁኔታን በእጅጉ ያሻሽላል። ሴትን የሚያበረታታ ማዕከል መገንባት ከልጆቻቸው ጋር እኩል እየተሰቃዩ ያሉ እናቶች ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ እድገትን ያመቻቻል። ይህም ሕፃናት እና እናቶች የተከበረ ህይወት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። የዚህ ህልም ፕሮጀክት እውን መሆን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ብዙ ልጆች እና እናቶቻቸው ጥያቄ መልስ ይሆናል።

በዚህ ቤት እናቶች የጤና ምርመራ አድርገው ልጆቻቸው ብዙም ሳይጎዱ ሊወለዱ የሚችሉበት ህክምና ሊኖር እንደሚችል የምትናገረው ሲስተር አሳየች፤ ማእከሉ ለድምፅ አልባዎቹ ድምፅ ሊሆን፤ ትኩረት ለተነፈጋቸው ትኩረትን ሊሰጥ ሰፊ ራይን ሰነቆ የሚሰራ መሆኑን ታስረዳለች።

## በዓል በሲስተሯ ቤት

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር ወደ ሁለት መቶ ስልሳ ለሚሆኑ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆችና እናቶቻቸው ይደግፋል። አሁንም የፋሲካ በዓልን አስመልክቶ ተደራራቢ የጤና ችግር ላለባቸው ከሁለት መቶ ሃምሳ እናቶች ውስጥ መቶ ሰባ አምስት ለሚሆኑ ሕፃናት እናቶቻቸው ዱቄት፣ ዘይት ዶሮ እና እንቁላል እንዲሁም አንድ ሺህ 500 ብር የኪስ ገንዘበ ስጦታን አበርክቷል።

ለስጦታው የሚሆን ገቢ የተገኘው ለተለያዩ ለጋሾች በቀረበ ጥያቄ ሲሆን፤ በተጨማሪም የኦቲዝም ቀንን አስመልክቶ በተዘጋጀ የማስ ስፖርት ማህበሩ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን በማግኘቱ በርካታ ሰዎች በራሳቸው ዶሮ እንቁላልና ገንዘበ አበረክተዋል። ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ በየአመቱ ለአዲስ አመትና ለፋሲካ በአላት ድጋፍ ስለሚያደርግ ለእናቶቹ የሚሰጠው ስጦታ አይነቱ በዛ እንዲል ሆኗል።

በአኬዥያ መንደር ውስጥ ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸው 18 ሕፃናት የሚገኙ ሲሆን፤ በጤና፣ በምግብ፣ በመጠለያ፣ በትምህርት እና የሥነ-ልቦና አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን እዛ ለሚገኙት ልጆች ለጋሾች የሚሰጡት የአመት በአል መዋያ፤ የወረዳ መስተዳድሩ የሚያመጡት በጎችና ሌሎች በዓል ማድመቂያዎች የሚደረጉ መሆኑን ተናግራለች።

ሲስተሯ እና ቤተሰቧ በዓልን የሚያከብሩት በግራር ማእከል ውስጥ መሆኑን የምትናገረው ሲስተር፤ በዓልን በመኖሪያ ቤቷ የምታከብረው ከአስር ሰአት በኋላ እንደሆነ ትናገራለች። በጠዋት ማእከሉ ውስጥ ያሉት ልጆች የበዓላት እለት ልብስ ለብሰው በጠዋት የደረሰውን ለበዓል ማደመቂያ የተዘጋጀ ምግብ በልተው የሚጀምሩ ሲሆን፤ እዛው ያሉ ልጆችና ሰራተኞች ዶሮም በግም መስራት ላይ አብረው ተሳታፊ እንደሚሆኑ ትናገራለች።

በተቋሙ ተደራራቢ የጤና ችግር ካላቸው ልጆች በተጨማሪ ጤነኛ ልጆች በመኖራቸው የተነሳ፤ ከበዓል ዋዜማ ጀምሮ ሽንኩርት መላጥ፤ ዳቦ መድፋት ሌሎች ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚደረግ መሆኑን ትናገራለች። ይህም የሚደረግበት ምክንያት ልጆቹ የራሳቸውን ህይወት ሲመሰርቱ ትዳር ሲይዙ የሚያውቁትን የበዓል አከባበር ቤታቸው እንዲተገብሩ የሚረዳቸው መሆኑን ታስረዳለች።

በበዓሉ ቀን ምሳ አብረው በልተው ቡና ተፈልቶ ዳቦ ተቆርሶ ማእከሉ ያሉ ልጆች ከተደሰቱ በኋላ የራሷን ቤት እንደምታስታውስ ታስረዳለች። በዚህ ስራ እሷ የበለጠ ተሳትፎ ቢኖራትም እህት ወንድሞቿ እና እናቷ ለበዓልም ሆነ ሌሎች ግዥዎች ላይ የቀኝ እጅ እንደሆኗት ትናገራለች። ቤተሰቦቿ ልጆች በሙሉ አጋር እንደሚሆኑም ትገልፃለች።

ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸውን ልጆች እጅግ አስቸጋሪዎች በመሆናቸው እነሱን ይዘው ያለ ምንም ገቢ የሚኖሩ እናቶችን መደገፍ የሁሉም ማህበረስብ ኃላፊነት ነው ትላለች። ሕፃናቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲገለሉ የኖሩ ሲሆን፤ የሚገባቸውን ድጋፍ እና እንክብካቤ ማግኘት አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ የጤና፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የስነልቦና ቀውስ ተጋላጭ ሆነዋል። ይህንን ለመቅረፍ ደግሞ ሁሉም ማህበረሰብ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ትላለች።

ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ማቆያ፣ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል እና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ኦሮሚያ ክልል ፣ ሸገር ከተማ፣ ፉሪ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 1 ልዩ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን፤ ላለፉት 17 ዓመታት አዲስ አበባን ጨምሮ በአራት ማዕከላት በማህበረሰብ ውስጥ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የኤች አይ ቪ ስርጭት ለመቀነስ ወደ 12 ሺህ ገደማ የኅብረተሰብ አካላትን ተጠቃሚ እያደረገ መቆየቱን በመጠቆም፤ ለቀጣይ ጊዜም በተሻለ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ማሰባቸውን ታብራራለች።

‹‹ማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን ተደራራቢ ችግር ለመቅረፍ መነሳት ጠንካራ ልብ የሚያስፈልገው ተግባር መሆኑ የማእድ መጋራቱ እለት ተገኝቼ የተመለከትኩ ሲሆን፤ በእለቱ ከልጆቻቸው ጋር በበዓሉ ላይ ተገኝተው የነበሩት እናቶች ለምርቃት ተነስተው ያለ ከልካይ ግድቡን ጥሶ የሚወርደውን እንባቸውን መመልከት ብቻ በቂ ነበር።›› ስትል ትናገራለች።

‹‹ምንም እርዳታ የመከፋታቸውን ጥግ ይዳስሰዋል ተብሎ በማይባል ልክ ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸውን ልጆች የያዙ እናቶች የሚያዝኑ መሆኑ በእለቱ ተመልክተናል።›› የምትለዋ ሲስተር አሳየች፤ የእነርሱ መኖር የልጆቻቸውን እስትንፋስ የሚያቆይላቸው የሚመስላቸው፤ የልጆቻቸውን መዳን በጉጉትና በተስፋ የሚመለከቱ፤ ድህነት በጠንካራ እጁ የሚደቁሳቸውን እናቶች መመልከት የሚያሳምም መሆኑንም ተናግራለች።

ሀዘናቸው ተጋብቶባት ልብ የሚናጥ ጠጋ ብሎ ስለችግራቸው ሲጠየቅ፤ አሳዛኝ ስሜት ውስጥ የሚከቱ እነዚህን ሰዎች ከፈጣሪ በታች ደጋግ ልቦች ያላቸው ሰዎች መኖራቸው መልካም መሆኑን በመጥቀስ እነርሱን ያበርክትልን ትላለች።‹‹ ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነውና ይህንን የማህበረስብ ችግር በመረዳት ሁሉም ማህበራዊ ኃላፊነቱን ይወጣ።›› በማለት መልዕክቷን አስተላልፋለች።

ተናግረው ማሳመን የማይችሉ፤ ለምነው ማግኘት አይደለም የተሰጣቸውን እንኳን በአግባቡ መጉረስ የሚሳናቸውን ማገዝ፤ ልብ በቅንነት ካልሰፋ የማይነካ ነውና በዓልን ከድምፅ አልባዎቹ ልጆቿ ጋር ያሳለፈችውን ይህችን ሴት በረከቷን ያብዛልሽ፤ ቅን ልብሽን አይቀይርብሽ በማለት የዛሬውን ፅሁፍ ቋጭተናል። ቸር ይግጠመን!

# ሳምንቱን በታሪክ

## ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ድል

ዋለልኝ አየለ



ዛሬ የአርበኞች ቀን ነው።የፋሲካ በዓል ቀኑ ስለሚቀያየር አጋጣሚ ሆኖ በዚህ ዓመት ከአርበኞች ቀን ጋር ተገጣጥሟል።በዚህም ምክንያት የዛሬው የአርበኞች ቀን ከዚህ በፊት በተለመደው ድምቀት እንደማይከበር ግልጽ ነው።ሌላው አጋጣሚ ደግሞ በዚህ ዓመት አዲስ አበባን የማስዋብ አካል የሆነው የኮሪደር ልማት የድል ሀውልት ያለበት ቦታ (አራት ኪሎ) በግንባታ ሥራዎች ምክንያት ለማክበር ምቹ አይደለም።በሁለቱም ምክንያቶች የዘንድሮው የአርበኞች ቀን በመገናኛ ብዙኃን ከዚህ በፊት በተለመደው ትኩረት ላይታወስ ይችላል።ለእምነቱ ተከታዮች ‹‹እንኳን ለትንሳኤ በዓል አደረሳችሁ!›› እያልን በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 83 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን እናስታውሳለን።ከዚያ በፊት ግን ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭሩ እናስታውስ።

የተጀመረበት ትክክለኛ ቀን ‹‹በዚህ ቀን ነው›› ባይባልም በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ እንቅስቃሴው የተጀመረው የሠራተኞች መብት ‹‹የላብ አደሮች ቀን›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶት በዚህ ሳምንት ተከብሯል።‹‹የላብ አደሮች ቀን፣ የወዝ አደሮች ቀን፣ የሠራተኞች ቀን...›› በሚሉ የአማርኛ ስያሜዎች የሚከበረው ይህ ቀን በውጭው ዓለም ደግሞ ‹‹ሌበር ዴይ›› እና ‹‹ሜይ ዴይ›› በሚሉ የእንግሊዘኛ ቃላት ይታወሳል።ሚያዚያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዕለቱ በዚሁ ዓምዳችን ዝርዝር ታሪኩን የሰራን መሆኑ ይታወሳል።

ሌላው የዚህ ሳምንት ክስተት፤ ከ135 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም የተፈረመውና ለዓድዋ ጦርነት ሰበብ የሆነው የውጫሌ ውል ነው።

የዉጫሌ ውል በአሁኗ አምበሳል ወረዳ ውጫሌ በምትባል ቦታ በአጼ ምኒልክና በጣሊያኑ ንጉስ ኢምቤርቶ ተወካይ ኮንት አንቶሎኒ መካከል ተፈረመ።ውሉ 20 አንቀጾች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ አንቀጾች ውስጥ ሰበበኛዋ አንቀጽ 17 ለጣሊያን የውርደት ካባ ያለበሰውን የዓድዋን ጦርነት አስከተለች፤ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ድል በማጎናጸፍ የጥቁርን ጀግንነት ያስመሰከረ ክስተት ሆነ።

አንቀጽ 17 በአማርኛ ‹‹የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከአውሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል›› የሚል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም የኢትዮጵያ መንግስት ከፈቀደ ወይንም ከፈለገ በኢጣሊያ በኩል ከውጭ መንግስታት ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሚችል የሚጠቅስ ነው።

የአንቀጹ የጣሊያንኛ ትርጉም ግን ‹‹የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ ሀገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካኝነት ማድረግ ይገባዋል›› የሚል ነበር።ይህም የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት በቀጥታ በጣሊያን በኩል እንዲከናወን የሚያስገድድ ነበር።

በአንቀጽ 17 አማካኝነት ጣሊያን የውሉን ሀሳብ በጣሊያንኛ በመቀየር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመገርሰስ የጣልያን ሞግዚት እንድትሆን ቀዳዳ እያበጀች ነው ብለው ነገሥታቱ እና መኳንንቱ ስለተገነዘቡ የውጫሌ ውልን እንደማይቀበሉት አሳወቁ።

የጣሊያን መንግስት ውሉን ለማፍረስ አሻፈረኝ በሚልበት ጊዜ፣ የውጫሌ ውል እንዲፈርስና ኢትዮጵያ ለማይቀረው ጦርነት እንድትዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ባለቤት የሆኑት እቴጌ ጣይቱ ብጡል እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል።

እቴጌዋ ‹‹እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም።ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ›› ብለው የተናገሩት እነሆ ታሪክ ሆኖ ይታወሳል!

ሌላኛው የዚህ ሳምንት ክስተት ከ88 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ሚያዚያ 27 1928 ዓ.ም ታዋቂው ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር ተወለደ።ደራሲ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር የታሪክና የማህበራዊ ጉዳዮች አዋቂ ቢሆንም ብዙዎች የሚያውቁት ግን ‹‹ትኩሳት›› እና ‹‹ሌቱም አይነጋልኝ›› በተሰኙ ሁለት መጽሐፎች ብቻ ሆኗል።በኢትዮጵያ ባህልና ወግ ባልተለመደ ሁኔታ በእነዚህ መጻሕፍት ወሲባዊ ቃላትን በመጠቀሙ ከሌሎች መጽሐፎቹ ይልቅ በእነዚህኞቹ አጀንዳ ሆነ።ያም ሆነ ይህ ስብሃት ገብረእግዚአብሔር ለየት ባለ የሕይወት ፍልስፍናው እና በስነ ጽሑፍ ሥራዎቹ ሲታወስ ይኖራል።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የአርበኞች የድል ታሪክ እናልፋለን።

በዓድዋ ጦርነት ሽንፈት የተከናነበው ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ዝግጅት አድርጎ ዳግም ወረራ ሞክሮ ነበር።ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በለመዱት የጀግንነት ስልትና ወኔ ባደረጉት ተጋድሎ ነፃነታቸውን አስከብረዋል።ይህ ድል የኢትዮጵያውያን የወታደራዊ ጀግንነት እና የቀዳማዊ አጼ

### የድል ሀውልት

ኃይለሥላሴ የዲፕሎማሲያዊ ጥበብ ውጤት ነበር ማለት ይቻላል።

የተክለ ጻድቅ መኩሪያ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ›› የባህሩ ዘውዴ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983›› መጽሐፎች በዝርዝር ይነግሩናል።

ኢትዮጵያ በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ሰንደቅ ዓላማዋ ከታጠፈ ፣ ሉዓላዊነቷ ከተደፈረ 5 ዓመታት በኋላ ነፃነቷን ያስመለሰችው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በ11 ሰዓት ንጉሰ ነገሥቱ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በአርበኞች ብርታትና መስዋዕትነት የጣሊያን ባንዲራ አውርደው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በታላቁ ቤተ መንግሥት ሲሰቅሉ ነው።

የሚያዝያ 27 የንጉሰ ነገስቱ አዲስ አበባ ገብቶ ሰንደቅ ዓለማ መስቀል ሌላው ታሪካዊነቱ ከአምስት ዓመታት አስቀድሞ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 በዚያው ቀን ወደ ኢትዮጵያ የዘመተው የጣልያኑ ጦር አዛዥ ጄኔራል ባዶሊዮ አዲስ አበባ ገብቶ በታላቁ ቤተ መንግሥት የጣሊያንን ባንዲራ የሰቀለበት ቀን መሆኑ ነው።ጣሊያን ከዓድዋ ሽንፈቷ 40 ዓመታት በኋላ በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በወታደራዊ ኃይል ይበልጥ ደርጅታ ኢትዮጵያን ከሦስት አቅጣጫዎች ወረረች።ከአድዋው ዘመቻ ያልተሻለ የጦር ትጥቅ የነበራት ኢትዮጵያም የጣሊያንን ጦር በፅናት ተዋጋች።

የወቅቱ ሃያላን እንግሊዝና ፈረንሳይ የጦር መሣሪያ በግዢ እንዳታገኝ ለጣሊያን ተደርበው ስላሴሩባት ኢትዮጵያ ብቻዋን ጦርነቱን በመጋፈጧ ድል ማግኘት አልቻለችም ነበር።

የየግንባሮቹ የኢትዮጵያ የጦር አዛዦች ብዙዎቹ ሞተው ሠራዊቱም በመርዝ ጋዝና በአውሮፕላን ቦምብ ተደብድቦ ያለቀው አልቆ የቀረው ቀርቶ ጣልያን ጊዜያዊ ድል አግኝታ ዋና ዋና ከተሞችን ብትቆጣጠርም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በገጠሩ ክፍል እምቢ ለነፃነቴ፣ እምቢ ለአገሬ ብለው የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ።ንጉሰ ነገስቱም ስደት ሄደው በጊዜው ለነበረው የመንግሥታቱ ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) አቤቱታ አቀረቡ።የሚሰማቸው ግን አላገኙም።የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ከቀን ወደ ቀን ድል እየተቀዳጁ የጣሊያን ወታደሮችን መፈናፈኛ ፤ መግቢያ መውጫ አሳጧቸው።

ከጣሊያን ወታደሮች ይማርኳቸው በነበሩ መሣሪያዎች ራሳቸውን እያደራጁ አብዛኛውን የገጠር ክፍል ተቆጣጠሩት።

በዚህ መሃል እንግዲህ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ለኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ ነበረው።ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲቀሰቀስ ጣሊያን የናዚ ጀርመን አጋር ሆነች።ያን ጊዜ እንግሊዞች የጣሊያን ጠላት ሆነው ኢትዮጵያን መደገፍ ጀመሩ።

ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥተው ፤ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ እረዷቸው።

በጄኔራል ካኒንግሂም የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከኬንያ ተነስቶ በደቡብ አቅጣጫ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ሲገሰግስ ፤ በጄኔራል ፕላት የሚመራው ጦር ከሱዳን ተነስቶ ወደ አሥመራ ፤ ከዚያም በሰሜን አቅጣጫ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ተንቀሳቀሰ።

በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ የሚመራውና የአርበኞችና የእንግሊዝ አማካሪዎች የሚገኙበት ‹‹ጌዲዮን›› ተብሎ የተሰየመው ጦር ከሱዳን ተነስቶ በኦሜድላ አልፎ በጐጃም በኩል ወደ መሐል አገር ገሠገሠ።

በመካከለኛው ኢትዮጵያ አርበኞች በጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃታቸውን አፋፋሙ።

ጣሊያኖች ክፉኛ ተሸነፉ።በየቦታው ድል የመሆናቸው ዜና ናኜ።

ዘመቻው ከተጀመረ ሁለት ወራት ሳይሞላው፤ ጣሊያኖች አዲስ አበባን ለቀው ፈረጠጡ።

መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም የጄኔራል ካኒንግሃም ጦር አዲስ አበባን ተቆጣጠረ።

እንግሊዞች ኢትዮጵያውያን አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ስላልፈለጉ ቀዳማዊ አጼ ኃይል ሥላሴን በደብረ ማርቆስ ለአንድ ወር ያህል እንዲቆዩ አደረጓቸው።

ይሁንና በአዲስ አበባ በአርበኞች ተፅዕኖና ቅሬታ የተነሳ አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ፈቀዱ።አፄ ኃይለ ሥላሴም ወደ አዲስ አበባ እንዲጓዙ ፈቀዱ።ንጉሰ ነገስቱም አዲስ አበባ በታላቁ ቤተ መንግሥት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ።አዲስ አበባ ገብተውም የሚከተለውን ንግግር አደረጉ።

‹‹ይህ የምትሰሙት ድምጽ የኔ የንጉሳችሁ የቀዳማዊ ሀይለ ሥላሴ ነዉ። አባቶቻችን ደማቸውን አፍሰው ዐጥንታቸውን ከስክሰው በነፃነት ያቆዩልን ሀገራችንን ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ ለማራመድ የምንደክምበት ጊዜ ከጥንት ዠምሮ ስለሆነ ደመኛ ጠላታችን ኢጣሊያ ይህንን እይታ ወሰናችንን ጥሳ የግፍ ጦርነት እንዳደረገችብን ሁላችሁም የምታዉቁት ነዉ። እኛም በተቻለን ከተከላከልን በኋላ ርዳታ ለመጠየቅ ወደ መንግስታት ማሕበር ወደ ወዳጆቻችን መንግስታቶች መጣን፤ እዚህ ስንነጋገር በቆዬንበት ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች ሰይፋችሁን ሳትከቱ ፊታችሁን ሳትመልሱ ሰንደቅ ዓላማችሁን ሳታጥፉ ለባዕድ አንገዛም በማለት በመሳሪያ ብዛት ከሚበልጣችሁ ጨካኝ ጠላት ጋር የባሕርይ የሆነዉን ዠግንነታችሁን መሣሪያ አድርጋችሁ በኢትዮጵያ አምላክ ብቻ ተማምናችሁ በዠግንነት ቀንና ሌሊት በዱር በገደል ስትጋደሉ ቆይታችሁ ይኸዉ አሁን እንደምታዩት የማያቋርጥ የአምስት አመት ትግላችሁ የድካማችሁንና የመሥዋዕታችሁን ፍሬ ለማየት እንድትበቁ አደረጋችሁ።

የሀገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ!

ዛሬ ኢትዮጵያ እጆቹዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ እልል እያለች ምስጋናዋን የምታቀርብበት ደስታዋንም ለልጆቿ የምትገልጽበት ቀን ነዉ። የኢትዮጵያ ልጆች ከባድ የመከራ ቀንበርና ከዘለዓለም ባርነት ነፃ የወጡበት ቀንና እኛም አምስት አመት ሙሉ ተለይተነው ከነበረው ከምንወደዉና ከምንናፍቀው ሕዝባችን ጋር ለመቀላለቀል የበቃንበት ቀን ስለሆነ ይህ ቀን የተከበረና የተቀደሰ በያመቱም ታላቁ የኢትዮጵያ በዓል የሚዉልበት ነዉ። በዚህም ቀን ለሚዎዷት ላገራቸዉ ነፃነት ለንጉሰ ነገሥታቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር ከአባቶቻቸው የተላለፈውን ጥብቅ አደራ አናስወስድም በማለት መስዋዕት ሆነው ደማቸውን ያፈሰሱትን አጥንታቸውን የከሰከሱትን ጀግኖቻችንን እናስታውሳለን። ለዚህም ለጀግኖቻችን የኢትዮጵያ ታሪክ ምስክር ይሆናል።

ባለፈው አምስት አመታት ውስጥ በዝርዝር ተነገረውና ተቆጥረው የማያልቁ ያገኘናቸው መከራና ስቃይ ትምህርት ሆነውን ሰራተኛነት አንድነት ህብረትና ፍቅር በልባችሁ ተጽፈው ለምናስበው ለኢትዮጵያ ጉዳይ ረዳቶች ለመሆን ዋና ትምህርት የሚሰጣችሁ ነው። በአዲሷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነጣጠሉ በሕግ ፊት ትክክልና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን። ሀገር የሚለማበትን ሕዝብ የሚበለጽግበትን እርሻ፣ ንግድ፣ ትምህርትና ጥበብ የሚሰፋበትን የሕዝባችን ሕይወቱና ሀብቱ የሚጠበቅበትን የሀገር አስተዳደርም በአዲሱ ስልጣኔ ተለውጦ ፍጹም የሚሆንበትን ይህን ለመሰለው ለምንደክምበት ስራ አብሮ ደካሚ መሆን አለባችሁ።

የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ድል አድርጎ ለመያዝ ችሎት ከሰጠው መሳሪያ በቀር ኢትዮጵያን ለመግዛት ሌላ ተስፋ ያደረገው ነገር ነበር ይኸውም የኢትዮጵያ የነገድ ልዩነት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ እርሱ ሃሳብ አንደኛው ወገን ከሴም ዘር የመጣው የትግሬና የሸዋ፣ የጎጃም፣ የበጌምድር፣ በጠቅላላው አማራ የሚባለው፣ ሁለተኛው በኢትዮጵያ ምዕራብና ደቡብ የሚገኙትን እነወለጋ፣ እነጅማ፣ እነሲዳማ፣ እና አሩሲ እነዚህን የመሳሰሉት ሀገሮች ከካም ዘር የመጡ በነገድም በቋንቋም በሃይማኖትም የተለያዩ ናቸው ። አንደኛው ወገን ቢያመልጥብኝ ሁለተኛውን ወገን ይዤ አጠፋዋለሁ የማለት ተስፋ ነበረውና ይህንንም ሊሰራበት እንደጣረ በጉልህ ታይቷል። ዳሩ ግን የ3ሺህ አመት ባለው የነፃነቱ ዘመን በታሪኩ ውስጥ ምንም የሚያሳፍር ገጽ የሌለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን አሳይቶ ለጠላቱ ሳይመች ቀረ።›› ብለው ነበር ንጉሡ።

ይሄ የኢትዮጵያውያን የድል ብስራት የሆነው የአርበኞች ቀን ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ነው።በዚህ ጦርነት ውስጥ ምላጭ ስቦ ጥይት ከተኮሰው አርበኛ በተጨማሪ በየቤቱ ሆኖ የተባበረውም ቀላል አልነበረም። በትግሉ ጊዜ የአርበኞች ዋናው ችግር ቀለብ ነበር። ቀለባቸውን የሚያገኙትም ከአርሶ አደሩ ቤት ነው። ይሄ ነገር የሚሆነው ታዲያ በግድም በውድም ነበር።ፈቃደኛ የማይሆን አርሶ አደር ካለ ፋኖ እስከማስማራትም ተደርሶ ነበር።በተለይም ከጠላት ጋር የሚያብሩ ሰዎችን ደግሞ እህላቸው እንዲዘረፍና ለሰራዊቱ ቀለብ እንዲሆን ተደርጓል።

ሰራዊቱ ‹‹ደረቅ ጦር›› እና ‹‹መደዴ ጦር›› ተብሎ ለሁለት ተከፍሎም ነበር።ደረቅ ጦር የተባለው ሙሉ በሙሉ ውጊያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ‹‹መደዴ ጦር›› የተባለው ደግሞ እንደ ሁኔታው የእርሻ ሥራ ላይ እንዲሰማራ ይደረጋል። ነገሩ ሲከፋ ግን አርበኞች ፍራፍሬ፣ ቅጠላቅጠልና የዱር አውሬ ሁሉ እየበሉ ተዋግተዋል።እናቶች ከሰራዊቱ ጋር አብሮ በመዝመት ምግብና ውሃ ከማቀበል በተጨማሪ ባህላዊ ህክምና እየሰጡ ሰራዊቱን ታድገዋል።የወደቀውን በማንሳት የቆሰለውን በመጠገን ተሳትፈዋል።ይህ የአርበኞች ቀን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የተጋድሎ ድል ነው ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በዚህ ሁኔታ ነፃነቷን ማስከበሯ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከአራቱ ልዕለ ኃያላን አገራት (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ እና ሩሲያ) ጋር ለውይይት እንዲትቀመጥ ክብር ሰጥቷታል።የአውሮፓውያን ቅኝ ተገዢ የነበሩ የአፍሪካ አገራት ዕጣ ፋንታ ምን ይሁን ተብሎ ሲመከር ኢትዮጵያ ግን የሚመከርባት ሳትሆን አብራ የምትማከር ነበረች።ሃሳቧን እንድታዋጣ የምትጠየቅ ነበረች።የአርበኞች ቀን የወታደርም የዲፕሎማሲም ድል ውጤት ነው!

# የዝነኞች ገጽ

# ሊያ – የሞዴሎች ቁና!!!

*ግርማ መንግሥቴ*

የዛሬው ገጻችን ስለ ኢትዮጵያዊቷ ዓለም አቀፍ ሡፐር ሞዴል፤ እአአ በጃንዌሪ 3፣ 1998 “ልእለ ኃያል” ለመሆን ስለ በቃችው፤ ተዋናይት፤ አክትረስ፤ እንዲሁም፣ በታዋቂነቷ እና በመልካም ተግባሯ የዓለም የጤና ድርጅት በእናቶች፣ አዲስ በሚወለዱ ሕፃናት እና የሕፃናት ጤና ጥበቃ የበጐ ፈቃድ አምባሳደር ስለሆነችው፤ የአልባሳት ዲዛይን አውጪነቷን፤ እንዲሁም፣ የመድረክ ንግሥትነቷን አስመልክተው ብዙ የተባለላት፤ በእውቅ ዓለም አቀፍ የፋሽን መጽሔቶች ላይ ለበርካታ ጊዜ የውጭ ሽፋን (ከቨር ስቶሪ) ላይ በዋናነት በመውጣት ስለምትታወቀው፤ በእ.አ.አ. 2007 አመት ከዓለማችን 11ኛ ከፍተኛ ተከፋይ ስለሆነችው (“ፎርብስ” እንደዘገበው) ሊያ ከበደ ይሆናል።

እ.አ.አ. ጃንዌሪ 3፣ 1978 አዲስ አበባ የተወለደችውን ሊያ፤ ትምህርቷን በሊሴ ገብረማርያም ስለ ተከታተለችው ሊያ፤ በTime's Style & Design እና የመሳሰሉት መጽሔቶች ላይ የሽፋን ቦታን በተደጋጋሚ ለመያዝ ስለ በቃችው ሊያ፤ እ.አ.አ. በ2003 ለ“Estée Lauder ኮስሞቲክስ” በ57 አመት ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ተወካይ በመሆን የ3 ሚሊዮን ዶላር ስምምነት ስለ ፈረመችው ሊያ፤ በፎቶ ትዕይንቶች ላይ ጎልተው ከሚታዩ ጥቂት የአፍሪካ ሞዴሎች አንዷ ስለሆነችው ሊያ፤ “ይህንን ስሜት የፈጠረብኝ አፍሪካ ውስጥ ተወልጄ ማደጌ ነው። በድህነት ተከበው እየኖሩ ስለድህነት አለማሰብ ፈፅሞ የማይቻል ነገር ነው። ልጅህን በምትወልድበት በዚያችው ደቂቃ ነው ለልጅህ የተሻለች ዓለም ትተህ ማለፍ እንዳለብህ ማሰብ የምትጀምረው” በሚለው ቋሚና ዘላቂ አባባሏ ዘወትር ስለ ምትነሳው ሱፐር ሞዴል ሊያ ከበደ የምንለውን ልንል ነው ዛሬ ወደዚህ አስታዋሽ ገጽ የመጣነው።

የግንቦት 10 ቀን 2010 የታይም መጽሔት እትም ላይ ዲዲዮር ድሮግባ፣ ስኮት ብራውን፣ ጀምስ ካሜሮን፣ ዛሃ ሀዳድ፣ ቤንስቴለር፣ አሽተን ኩቸር፣ ሣራ ፖሊን፣ ቢል ክሊንተን፣ ካትሪን ቢግሎው፣ ሳንድራ ቡሎክ፣ ሳይመን ኮዌል፣ ሀን ሀን፣ ኦፕራ ዌንፍሬይ፣ ባራክ ኦባማ እና ሌሎችም ተርታ በመሰለፍ በፎርብስ መጽሔት ላይ ከ100 ተፅእኖ ፈጣሪዎች አንዷ የሆነችው ሊያ፤ በአንድ ወቅት 2.5 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በማግኘት ከዓለማችን 15 ከፍተኛ ተከፋይ ሡፐር ሞዴሎች መካከል 12ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠችው ሱፐር ሞዴል ሊያ፤ The Good Shepherd እና Lord of War የተባሉ የሆሊውድ ታላላቅ ፊልሞች ላይ በመለስተኛ ተዋናይነት ስለ ተሳተፈችው ሊያ ከበደ ጥቂት ለማለትና ዝናዋን ዳግም ለማንገስ በማሰብ ዛሬ ወደዚህ ውለታ ከፋይ ገጽ ብቅ ብለናል።

የፊልሙ መነሻ ድርሰት፣ ሶማሊያዊቷ ዋሪስ ዳሪ ከጻፈችው ግለታሪኳ የተወሰደ ሲሆን፣ መጽሐፉ በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ በከፍተኛ ቁጥር በተሸጠው፤ በ2009 እ.አ.አ በተለቀቀውና በአፍሪካ ሴቶች ላይ የሚፈጸመው ግርዛት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት መሆኑን በቁጭት የሚያሳየው፤ በራሷ በዋሪስ ዳሪ በተዘጋጀውና የጀርመንና የአሜሪካ ዜግነት ባላት የፊልም ዳይሬክተር በተቀናበረው፤ ቀረፃው በጅቡቲ፣ በኒውዮርክ፣ በኮለኝና በሙኒክ ከተማዎች The Desert Flower (የበረሃዋ አበባ) በተሠኘው ፊልም ላይ የቀድሞዋን ሡፐር ሞዴል Waris Dirieን በመሆን በመሪ ተዋናይትነት በመሳተፍ ከፍተኛ ዕውቅናን ያገኘችው ሊያ በእርግጥም አድናቂዎቿን ብቻ ሳይሆን እማያውቋትን ሁሉ እጃቸውን አፋቸው ላይ ያስጫነች፤ ከልዩም ልዩ ነችና አድናቆት ሲያንሳት እንጂ ሊበዛበት አይችልም።

በ2008 የሀበሻ እጅ ጥበብ ያረፈባቸውን የሕፃናትና የሴቶችን ልብሶችን የሚያመርተውን “የሊያ ከበደ የልብስ አምራች ድርጅት” (http://www.lemlem.com/ በሚል የዘረጋችውን ድረ-ገፅ ይጎብኙ) የከፈተችውን ሊያ፤ “ሰዎችን እንደመርዳት” የሚያስደስታት ነገር የሌላት ሊያ፤ የሀገሯን ባህል ለማስተዋወቅ ለአፍታ እንኳን የማትታክተው ሱፐር ሞዴል ሊያ፤ እ.አ.አ. በ2000 የhedge fund ማናጀር ከሆነው ባለቤቷ፣ ኬሲ ከበደ ጋር በትዳር የተሳሰረችውና ሁለት ልጆችን (ስሁል (ወንድ) እኔ ሴቷ ሬይ) ያፈራችው ሊያ አስቀድሞ የሞዴሎች ሁሉ ቁና መሆኗ የተመሰከረላት ናትና እዚህ ስናነሳት በኩራት ይሆናል።

ከጅምሩ፣ የሕይወት መስመሯን (ከአንድ የፓርሺያ ኤጀንሲ ጋር) ከአዲስ አበባ ወደ ፈረንሳይ፤ ከፈረንሳይ ወደ ኒውዮርክ ያደረገችው ሊያ፤በጣልያን፣ ጃፓን፣ አሜሪካ፣ ስፔን፣ ፈረንሣይ ሀገራት የተለያዩ ስመጥር የህትመት ውጤቶች ላይ የፊት ሽፋን ቦታን በተለያዩ ጊዜያት ያገኘችው ሱፐር ሞዴል ሊያ፤ የፋሽን ኢንዱስትሪውን ተቀላቅለው የጥቁሮችን ማንነት እና ባህል ለዓለም በመግለጽ በኩል ከተሳካላቸው ምርጥ የአፍሪካ ዲዛይነሮች መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ ዓለም አቀፍ ሱፐር ሞዴል እና ዲዛይነር ሊያ ከበደ የሱፐሮች ሱፐር ነችና ለዛሬ ማንሳታችን ስለ ክብሯና ሀገሯን ስለ ማስጠራትና ማስከበሯ መሆኑን ስንገልጽ ደስታችን ወደር የለውም።

የጤና ባለሙያዎችን ማሠልጠን እና በገንዘብ መደገፍ ላይ ያተኮረው የሊያ ከበደ ፋውንዴሽን መስራች፤ በቅርቡም አዋላጅ ነርሶችን ከሚያሰለጥነው አመርፍ ኸልዝ አፍሪካ ከተባለው መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በአጋርነት እየሰራች የምትገኘው ሊያ ሲነሳ፤ በኒውዮርክ የምትኖረው ሊያ የእውቅ ኩባንያዎች ሞዴል ሆና ከመስራቷም ባሻገር በፓሪስ፣ ለንደንና ኒውዮርክ የሞዴል ሾው መድረኮች ላይ ስለተምነሸነሸችው ሊያ ሲነሳ፤ ከ2007 ዓ.ም ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ከፍታ፤ በተለይ ሴት የጥልፍ ባለሙያዎችንና ሸማኔዎችን እያገዘች ስለምትገኘው ሱፐር ሞዴሊስት ሊያ ሲነሳ ወዘተ ለዝነኝነትዋ መሰረቱ ሞዴሊስትነቷ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ ተግባሯም ነውና ሊያ ልዩ ነች ስንል ያለ ምክንያት አይደለም።

እ.አ.አ. በ2003 ለEstée Lauder ኮስሞቲክስ በ57 አመት ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ተወካይ በመሆን የ3 ሚሊዮን ዶላር ስምምነት የፈረመችው፤ በ2000 የትዳር አለምን የተቀላቀለችው ሊያ ከአንጋፋው የፋሽን መጽሔት «ቮግ» (በ2019) ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጋ በነበረችበት ወቅት እስከ 18 አመቷ ድረስ በአዲስ አበባ እንዳደገችና ከዚያም ወደ ፓሪስ እንደ ሄደች በቃለምልልሷ ገልፃለች። ከዛስ?

ከአንድ አመት በኋላ በመጀመሪያ ቺካጎ፤ ቀጥላም ኒውዮርክ በመሄድ የሞዴሊንግነት ስራ ላይ መሰማራቷን ያስረዳችው ሊያ፣ በ2007 እ.ኤ.አ ወደ አዲስ አበባ ተመልሳ በመምጣት የተመለከተችውን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ «ለምለም» የተሰኘን ድርጅት በመክፈት ለበርካታ ሴቶችና የሽመና ባለሙያዎች የስራ እድል የፈጠረችው ሊያ ከበደ እውነትም ከባድ ሚዛን ነች ቢባል ቢያንስ እንጂ ከቶም ሊበዛ አይችልምና “ይበል!!!” ልትባል የግድ ይሆናል።

«ለምለም» ከዓለም አቀፉ «ዘውል ማርክ ካምፓኒ» ጋር በጋራ ለመስራት በመፈራረሙ ምክንያት በታዋቂው የአውስትራሊያው ብራንድ አማካኝነት ምርቶቹ በመሸጥ ላይ መሆናቸው ሲታወስ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴት የጥልፍ ባለሙያዎች የስራ እድል ማግኘታቸውና ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መቻላቸው ሲሰማ፣ የሞዴሎች ሁሉ ቁና ከመሆኗም በዘለለ ስለ ታዋቂ ኢትዮጵያዊቷ ሡፐር ሞዴል ሊያ ከበደ በጎ አድራጊነት ሳይመሰክሩ ማለፍ አይቻልም።

“ለምለም” ድርጅት ከአለም አቀፉ «ዘውል ማርክ ካምፓኒ» ጋር በጋራ ለመስራት በመፈራረሙ ምክንያት አሁን የለምለም ምርቶች በዚህ ታዋቂው የአውስትራሊያው ብራንድ አማካኝነት በመሸጥ ላይ መገኘታቸው መነሻና ምክንያቱ ሊያ እንጂ ሌላ ማንም አለመሆኑ ሲታወቅ፣ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ሡፐር ሞዴል፣ ተዋናይት፣ የልብስ ዲዛይነር፤ እንዲሁም፣ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የአለም የጤና ድርጅት በእናቶች፣ አዲስ በሚወለዱ ሕፃናት እና የሕፃናት ጤና ጥበቃ አምባሳደር ሊያ ከበደ እውነትም የጀግኖች ሁሉ መስፈሪያ ናትና አድናቂዎቿ ስለ አርአያነቷ ወደር የለሽነት ደጋግመው ቢያወሩ ማንንም ሊገርም አይገባም።



ከሰብአዊ ተግባሮቿ ለጊዜው ዞር እንበልና ወደ ጥበብ ስራዎቿ እንመለስ።

የእናቶችን ሞት ለመቀነስ፣ የጤና ባለሙያዎችን ማሠልጠን እና በገንዘብ መደገፍ ላይ የሚያተኩረውን “ሊያ ከበደ ፋውንዴሽን” በመመስረት ትኩረት ሰጥታ በመስራት ላይ ስላለችው፣ ስለ ሊያ ከበደ ከተመሰከሩላት በርካታ ምስክርነቶች ውስጥ የተለያዩ ጥበባዊ ተሳትፎና ስኬቷን በተመለከተ የሰፈሩ ሃሳቦችን እናገኛለን። ከእነዚህም መካከል ሊያ በተለያዩ ኪነጥበባዊ ስራዎች ውስጥ የተሳተፈች ሲሆን፤ እንደ The Good Shepherd እና Lord of War የተባሉ የሆሊውድ ታላላቅ ፊልሞች ላይ እንደ አነስተኛ ተዋናይነት፤ እ.አ.አ. በ2009 የተለቀቀው Desert Flower የተሠኘው ውስጥ በመሪ ተዋናይትነት የቀድሞዋን ሡፐር ሞዴል Waris Dirieን በመሆን የተሳተፈችበት ፊልም ከፍተኛ ዕውቅና እንድታገኝ ያስቻላት መሆኑ ነው።

ከላይ በጨረፍታ የጠቀስንላት፣ በደራሲዋ፣ በራስዋ በዋሪስ ዳሪ ተዘጋጅቶ በአፍሪካ ሴቶች ላይ የሚፈጸመው ግርዛት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት መሆኑን የሚያሳያው ፊልም ላይ መስራቷም ከዚሁ ከኪነጥበብ ተሳትፎዋ ጋር አብሮ የሚጠቀስ ነው።

በፓሪስ፣ ኒውዮርክ እና ለንደን የፋሽን መድረኮች ላይ ስራዎቿን የማቅረብ ልምድ ያላት ዓለም አቀፍ ሞዴል ሊያ ከበደ በግሏ የምታስተዳድረው ሳይት (http://liyakebede.com/) ያላት ሲሆን፤ ድረ-ገፁ የራሷን ማስታወቂያ እና የዕርዳታ ጥሪዎችን ለማስተላለፊያነት የምትጠቀምበት መሆኑንም ለጠየቃት ሁሉ ትናገራለች።

የአፍሪካ፣ የጥቁር ባህል እና ማንነት መናኸሪያ መሆኗ፤ የፋሽን ኢንዱስትሪውን ተቀላቅለው የጥቁሮችን ብዝሀነት እና ባህል ለዓለም በመግለጽ በፋሽኑ ዓለም ከተሳካላቸው ምርጥ 14 የአፍሪካ ዲዛይነሮች መካከል አንዷ መሆኗ፤ የአፍሪካ ሀገራትን የባህል አልባሳት በዋናነት በማስተዋወቅ ዓለም አቀፉ የፋሽን ገበያውን ሰብሮ እንዲገባ ስለማድረጓ በአድናቆትና አግራሞት የሚነገርላት ሊያ ከበደ በአፍሪካዊነቷ ድርድር የማታውቅ መሆኗም ሳይነሳ የማይታለፍ ማንነቷ ነው።

ትልቁ ወደ ሆነው የሕይወቷ ምዕራፍ የተሸጋገረችው ቶም ፎርድ የተባለ ግለሰብ Gucci ለተባለ የክረምት ፋሽን ትርኢት እ.አ.አ 2000 ላይ እንድትካፈል ከጠየቃትና ከተካፈለች በኋላ ሲሆን፤ እውቅናዋ እጅጉን የጨመረው በእ.አ.አ 2002 Paris Vogue መጽሔት እትም የውጭ ሽፋን ከሰጣት እና ሙሉ ይዘቱን ማለት በሚቻል ደረጃ ስለ እሷ ካደረገ በኋላ መሆኑ ስለ ሊያ ሲነገር ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነው። (በመጽሔቱ የጣሊያን፣ ጃፓን፣ አሜሪካ፣ ስፔን፣ ፈረንሳይ እትሞች ላይ መውጣቷም ከሌሎች መሰል የሙያ ባልደረቦቿ በተለይ ይጠቀስላታል።)

በሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ገጠመኛቸው ምክንያት አንድ የፊልም ዳይሬክተር አይቷት፤ አይቶም ተረድቷት፤ ተረድቷትም (የዛሬ ማንነቷን አስቀድሞ ተንብዮ) በፈረንሣይ ከፓርሺያው የሞዴል ኤጀንሲ ጋር ያገናኛት ስለ መሆኑ ስለ እሷ፣ ሱፐር ሞዴል፣ ፋሽን ዲዛይነር እና ተዋናይት ሊያ ከበደ በተነገረ ቁጥር በቀዳሚነት የሚጠቀስ በር ከፋች ገጠመኟ ነው።

በnetworthpost.org ላይ ይፋ እንደተደረገው፣ ዓለም አቀፍ ሱፐር ሞዴል ሊያ ከበደ በያዝነው 2024 የተጣራ ሀብት $18 ሚሊዮን (ዜናው “Liya Kebede Net Worth $18 Million” ሲል ነው የዘገበው) ያላትና የተሰማራችበትን የሙያ ዘርፍ በቁንጮነት እየመራች ያለች፤ እንቁ ኢትዮጵያዊት ዓለም አቀፍ ሞዴል ነች።

በ2013 የGlamour Award for The Role Models አሸናፊ፤ እንዲሁም ግንቦት 10 ቀን 2010 ታይም መጽሔት “ተፅዕኖ ማሳደር ከሚችሉ 100 የዓለማችን ምርጥ ሰዎች (The 100 most INFLUENTIAL PEOPLE IN THE WORLD) ብሎ ካወጣቸው ታዋቂ ሰዎች መካከል አንዷ ለሆነችው፣ እውቁ ዎልማርክ ኩባንያ አዘጋጅቶት በነበረው ዓለም አቀፍ ውድድር ላይ ዳኛ በመሆን ለዳኛቸው፤ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ ስላላት ሊያ ከበደ የበለጠ ስኬትን በመመኘት ለዛሬ በዚሁ አበቃን።

# ስፖርት





# በደጋፊዎች ደም የቆመ ክለብ

**ብርሃን ፈይሳ**



ደጋፊዎች ያላቸውን ሁሉ ሰጥተው የክለባቸውን ህልውና ማስቀጠላቸው የተለመደ ነው።በእርግጥም የየትኛውም ክለብ የደም ስሮች ናቸው ደጋፊዎች፤ ነገር ግን ከገንዘብ፣ ጊዜ እና ጉልበት ድጋፍ ባለፈ ደም እና ወዛቸውን ከፍለው ማቆማቸው እንግዳ ነገር ነው።ይህንን ያህል መስዋዕትነት ተከፍሎለት በህይወት ሊቆይ የቻለው ይህ የእግር ኳስ ክለብ ደግሞ የጀርመኑ ዩኒየን በርሊን ይሰኛል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ተወዳጅ ስፖርት ለሆነው እግር ኳስ በርካቶች መስዋዕትነት መክፈላቸው የተለመደ ነው።ነገር ግን ደጋፊዎች በዚህ ልክ አንድ ሆነው ለክለባቸው በመቆም ምስራቅ ጀርመናዊያኑን የሚስተካከላቸው የለም።‹‹ብረቶቹ›› የሚል ቅጽል ስም ያላቸው እነዚህ ደጋፊዎች ስለክለባቸው ፍቅር ሲሉ ሁሉን ሰጥተው ቀስ በቀስ እየሞተ የነበረውን ክለባቸውን ታድገው በትንሳኤ ከትልልቆቹ የአውሮፓ ክለቦች እኩል እንዲጠራ አድርገዋል።

እአአ በ1906 ምስራቃዊ በርሊን ላይ የተመሰረተው ይህ ክለብ በወቅቱ ስመጥር የነበረ ሲሆን፤ የቀዝቃዛውን ጦርነት ወቅት ጨምሮ በጀርመን ሊግ ቆይታው ቻምፒዮንም ነበር።የጀርመንና የዋና ከተማዋ በርሊንን ውህደት ተከትሎም በቡንደስሊጋው ሁለተኛው ዲቪዚዮን ሲጫወት የቆየ ክለብ ነው።የክለቡ መገልገያ የሆነው አልተን ፎርስትሪ ስታዲየምም በሀገሪቷ ታዋቂ ከሆኑት መካከል አንዱ በመሆኑ ከእግር ኳስ ያለፉ ሌሎች ሁነቶችንም ያስተናግዳል።በዚህ ሁኔታ የቆየው ክለቡ እአአ በ2004 የገጠመው የገንዘብ ኪሳራ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለዓመታዊ የውድድር መመዝገቢያ ክፍያ እስከማጣት አድርሶት ነበር።በወቅቱ የጀርመን እግር ኳስ ማህበር ለሚያደርገው ምዝገባ ክፍያውን ፈጽሞ በእንቅስቃሴ ላይ ለመቆየትም 1ነጥብ5 ሚሊዮን ፓውንድ ያስፈልገው ነበር።

ታዲያ በዚህ ወቅት ደጋፊዎች ከሚወዱት ክለባቸው ፊታቸውን ከመመለስ ይልቅ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መከሩ።እናም ይህንን የገንዘብ ችግር ቀርፎ የክለቡን አቅም ለማጠናከር ያስችላል ላሉት መላ ጊዜ ሳይፈጁ ተሰለፉ።በቀይ ማሊያ ለባሾች የተደረገው ይህ ረጅምና ቀልብ ሳቢ ሰልፍም ደም የመለገስ ነበር።በሀገረ ጀርመን ደም መለገስ ገንዘብ የሚያስገኝ ተግባር በመሆኑ ደጋፊዎች ለክለባቸው ያላቸውን ፍቅር ሳይሰስቱ በማበርከት ገንዘቡን በቀጥታ ትግል ላይ ለሚገኘው ክለባቸው ገቢ አደረጉ።‹‹ለክለባችን እንድማ›› የሚለው ይህ መፈክርም ለአንዴ ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ በተግባር ላይ እየዋለ ክለቡን በገንዘብ እጦት ከመፍረስ ታድጎታል።

በዚህ ሁኔታ የሚገጥሙትን አስቸጋሪ አካሄዶች ያለፈው ክለቡ እአአ በ2007/8 የውድድር ዘመን ደግሞ ሌላ ዱብ እዳ ደረሰበት።ይኸውም እአአ ከ1920 አንስቶ ግልጋሎት ሲሰጥ የቆየው ስታዲየማቸው አልተን ፎርስትሪ የመናድ አደጋ ማስተናገድ ጀመረ።ዘመናዊውን ዓለም የማይመጥነውና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ደረጃንም በማያሟላው የስታዲየሙ ወቅታዊ ሁኔታም ክለቡ ፈቃዱን ሊነጠቅና ከነበረበት ደረጃም ዝቅ ሊል እንደሚችልም በደጋፊዎቹ ዘንድ ስጋት አሳደረ።ሁሌም ለክለባቸው ቀድመው የሚሰለፉት ደጋፊዎች ከኪሳቸው የገንዘብ መዋጮ ቢያደርጉም ለደረሰበት ጉዳት በቂ ሆኖ አልተገኘም።አስገራሚዎቹ ደጋፊዎች ስለ ዩኒየን በርሊን የማይሆኑት የለምና ሌላ ዘዴ አፈለቁ፤ 2ሺ የሚሆኑትም በበጎ ፈቃደኝነት መዶሻና ሚስማር ጨብጠው ወደ ግንባታ ገቡ።

ምናልባትም ሃሳቡ ቀልድ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ቸልተኝነት የማያውቃቸው ደጋፊዎች ያሰቡትን እውን በማድረግ ለዓመታት ላባቸውን በማፍሰስ ለመደርመስ ጥቂት የቀረውን ስታዲየም አንጸው ዳግሞ ከእነግርማ ሞገሱ አቆሙት።አሁን ላይ በዋና ከተማዋ በርሊን በግዝፈቱ ሁለተኛ ደረጃን የያዘው ስታዲየሙ የሙዚቃ ድግስን ጨምሮ ታላላቅ መርሀ ግብሮችም ይስተናገዱበታል።ስታዲየሙ በዘመናዊ ሁኔታ ደረጃውን ጠብቆ ከመገንባቱ ባለፈ ሜዳውም ወቅቱን በዋጀ ሁኔታ ተሰርቶ መጠናቀቁን ተከትሎ ክለቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጨዋታውን ከሊፕዚንግ ጋር ሲያደርግ በስፍራው የነበረው ድባብ እጅግ አስደማሚ ነበር።በደጋፊው ጥንካሬ ከወደቀበት የተነሳው ክለቡ በውድድሩ አስደናቂ ተሳትፎ በማድረግ ውለታውን በተግባር በመመለስ ላይም ይገኛል።

ከ45ሺ በላይ የተመዘገቡ ደጋፊዎች ያሉት ዩኒየን በርሊን እአአ በ2019 ቡንደስሊጋውን የመቀላቀል እድል ሲያገኝ፤ በ2021 ደግሞ በአውሮፓ ኮንፍረንስ ሊግ ሰባተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል።በቀጣዩ ዓመት በዩሮፓ ሊግ አምስተኛ ደረጃን ሲይዝ፤ በቡንደስሊጋው አራተኛ ሆኖ ማጠናቀቁን ተከትሎ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ እስከመሳተፍ የደረሰ ብቃቱን ማሳየት ችሏል።ታሪኩን የሚያውቁ የእግር ኳስ አፍቃሪያንም ‹‹ክለቦች ያለ ደጋፊ ሊቆሙ አይችሉም፤ የዩኒየን በርሊን ደጋፊዎች ግን ለሌሎች ምሳሌ ናቸው›› ሲሉ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።




# ልጆችና የትንሳኤ በዓል

**እየሩስ ተስፋዬ**

የክርስትና እምነት ተከታይ ለሆናችሁ እና ለቤተሰቦቻችሁ ‹‹እንኳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ በዓል (ፋሲካ) በሠላም አደረሳችሁ›› ማለት እንወዳለን። እናንተም ‹‹እንኳን አብሮ አደረሰን!›› እንዳላችሁን አንዳችም ጥርጥር የለንም። ታዲያ ልጆችዬ በዓሉን እንዴት እያሳለፋችሁት ነው? የትንሳኤ በዓልስ ለምን እንደሚከበር ታውቃላችሁ?

ልጆችዬ! የሃይማኖት አባቶች ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ የሰው ልጆች የሠሩትን ሀጥያት ይቅር ለማለት በዕለት አርብ ተሰቀሎ፤ በራሱ ስልጣን ከሙታን መካከል ተለይቶ እሁድ ዕለት በሦስተኛው ቀን መነሳቱን ምክንያት በማድረግ የትንሳኤ በዓል በደማቁ እንደሚከበር ያስረዳሉ። ይህንን በማሰብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የሃይማኖት አባቶች እና ምዕመናን ነጭ ለብሰው ሌሊቱን በቅዳሴ እና በተለያዩ መንፈሳዊ መርሃ ግብሮች ያከብሩታል። በሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድም በዓሉን ‹‹ስለ እኛ የተከፈለ መስዋዕትነት እና ቤዛነት ነው።›› በማለት በዝማሬ እና በአምልኮ በደመቀ ሁኔታ ያከብሩታል።

በትንሳኤ በዓል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሠው ልጆች ቤዛ የሆነበት፣ ፍቅሩን እስከ ሞት ድረስ የገለጸበት እንደሆነ በሊቃውንቱ ይገለፃል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል እርሱ ሞቶ ሕይወትን የሰጠበት፣ ፍቅሩን የገለጸበት በመሆኑ፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች ችግረኞችን በመርዳት ፣ በመዋዳድ፣ በፍቅር፣ በሠላም እና በአንድነት በመሆን በዓሉን ማክበር እንዳለባቸው ያሳስባሉ።

ልጆችዬ! ምንም እንኳን ይህ በዓል መሠረቱ ኃይማኖታዊ ቢሆንም በሀገራችንም ሆነ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ዕለቱን ከመንፈሳዊ ክዋኔዎች ባሻገር በተለያዩ መንገዶች ያከብሩታል።




በሀገራችንም እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለያዩ ምግብና መጠጦች ይዘጋጃሉ። ድፎ ዳቦ በመጋገር፣ ዶሮ ወጥ እና ሌሎች ምግቦች በማዘጋጀት ፣ ቤታቸውን አስውበው ቄጤማ ጎዝጉዘውና እና አሳምረው ከዘመድ አዝማድ ጋር በመሆን በተለየ ደስታ ያከብሩታል። ልጆችዬ! የእናንተም የበዓል አከባበር ከላይ እንደጠቀስነው አይነት እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

በዚህ በዓል ታዲያ ወላጆች (አሳዳጊዎች) ለልጆቻቸው አዳዲስ ልብሶችን በመግዛት አቅማቸው ካልፈቀደ ወይም ዕቅዳቸው ካልሆነ ደግሞ ያላቸውን ልብስ እና ጫማ አጥበው እንዲሁም አሳምረው በማልበስ በዓሉን በደስታ ደምቀው እንዲያከብሩ ያደርጋሉ። ወላጆችም በተመሳሳይ መንገድ ራሳቸውን አስውበው እና አስጊጠው በዓሉን በቤታቸው ሰብሰብ ብለው፣ ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ከቅርብ ቦታ ራቅ እስካለ ቦታ በመሄድ፣ ዘመድ አዝማድን ‹‹እንኳን አደረሳችሁ?›› በማለት በታላቅ ድምቀት እንደሚያከብሩት ተመልክታችኋል ብለን እናምናለን። እናንተም በቤታችሁ ሰብሰብ ብላችሁ አልያም ወደ ወላጆቻችሁ ቤተሰቦች ጋር በመሄድ ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› ብላችሁ እና ተብላችሁ፣ ተመርቃችሁ እና ደስ ብሏችሁ በዓሉን በደስታ እንደምታሳልፉ ተስፋ አደርጋለሁ።

ልጆችዬ የትንሳኤን በዓል ጨምሮ በሌሎች በዓላት ላይ የተለያዩ ምግቦች፣ ኬኮች፣ ከረሜላዎች፣ ለስላሳ እና ሌሎች መጠጦች ይዘጋጃሉ። ታዲያ እናንተም ስትመገቡም ሆነ ስትጠጡ በመጠኑ እና በጥንቃቄ መሆን ይኖርበታል። ምናልባትም ‹‹ይህን ባናደርግ ምን እንሆናለን?›› የሚል ጥያቄ ታነሱ ይሆናል። ለምን መሠላችሁ ልጆችዬ? አብዝቶ መመገብ ከመጠን ላለፈ ጥጋብ ወይም ለምኞት ማጣት ይዳርጋችኋል። እንዲሁም ቅባታማ ምግቦች እና ሌሎች ምግቦች የሆድ ህመም ሊያመጣባችሁ ይችላል። ይህንን ካደረጋችሁ ግን በዓሉን በደስታ ከማሳለፍ ይልቅ በጭንቀት እና በህመም እንድትውሉ ትገደደላችሁ ማለት ነው። ስለዚህም በመጠን እና በጥንቃቄ መመገብ ይኖርባችኋል። ደግሞም ልጆችዬ በበዓላት ቀን ብቻ ሳይሆን ሁሌም ይህን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባችኋል።

ሌላው ልጆችዬ ከቦታ ቦታ በምትንቀሳቀሱበት ጊዜ የመኪና አደጋም ሆነ ሌላ ችግር እንዳያጋጥማችሁ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጉ። ወላጆቻችሁ ወይም ቤተሰቦቻችሁ የሚሏችሁንም ስሙ እሺ! ልጆች። ‹‹እሺ›› አላችሁ አይደል? በጣም ጎበዞች።

ዛሬ በዓል ስለሆነ አጠር እናድርገው አይደል? መልካም። ልጆችዬ! የሃይማኖት አባቶች ሁሌም እንደሚሉት በዓሉን በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡ ወገኖችን በመደገፍ እና በመንከባከብ ማሳለፍ ይገባል አይደል? ‹‹እንዴ! በሚገባ እንጂ! » የሚል ምላሽ እንደምትሰጡኝ ተስፋ አለኝ። እናም የተቻላችሁን መደገፍ ይኖርባችኋል። የቻላችሁትን ለመርዳት ግን ከወላጆቻችሁ ጋር መመካከር እና መነጋገር ይኖርባችኋል። ልጆችዬ በድጋሚ መልካም የትንሳኤ በዓል ይሁንላችሁ።